ጉባኤ ቃና

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ለግቢ ጉባኤ ተማሪዎች

ጉባኤ ቃና ፲፭ኛ ዓመት ቁጥር ፩

የካቲት ፳፻፲፮ ዓ.ም.

"አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ጸንተህ ኑር"

(፪ጢሞ. ፫፥፲፬)

ጉባኤ ቃና

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ለግቢ ጉባኤ ተማሪዎች

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/ ማኅበረ ቅዱሳን በግቢ ጉባኤያት አገልግሎት ማስተባበሪያ በሚዲያና ቴክኖሎጂ ዋና ክፍል በተለይ ለፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ለግቢ ጉባኤያት) በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ የሚወጣ መንፈሳዊ መጽሔት፡፡

የካቲት ፳፻ ዓ.ም. ተጀመረ

አሳታሚ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/ ማኅበረ ቅዱሳን

011 8 68 47 19 / 011 1 11 88 07/

ማውጫ

መልእክት

አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር 2

ስብከት

እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት 4

ትምህርተ ሃይማኖት

ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም መጥተዋልና.............11

የጥያቄዎቻችሁ መልስ

በግቢ ጉባኤ ውስጥ መሳተፍ ቤተ ክርስቲያንን እና ሀገርን ለማገልገል መሠረት የምንጥልበት ጊዜ ነው...19

ዓምደ ወራዙት

ባልንጀራ...28

ኪነጥበብ

መሰናክል..36

ከፍተኛ ሪፖርተር

እንዳለ ደምስስ

የገጽ መልክ/ሌይ አውት/

እና የሽፋን ገጽ ዲዛይን

ልደት አስፋው

ማኅበረ ቅዱሳን እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህንን ስያሜ አግኝቷል፡፡

“አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ጸንተህ ኑር”

(፪ጢሞ. ፫፥፲፬)

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰዎችና የመላእክት፣ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ምእመናን፣ በዓለመ ሥጋ እና በዓለመ ነፍስ ያሉ፣ የሥውራንና የገሃዳውያን አንድነት ናት። “በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” (ኤፌ. ፪፥፳) እንዲል።

ከልጅነት ጀምሮ የቃሉን ትምህርት ተምረን፣ በኪዳን፣ በቅዳሴው ዜማ እና መልእክት ተመስጠን፣ እንደ መላእክቱ ዘምረንና አመስግነን፣ የአምላካችን ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም እየተቀበልን ያደግንባትን፣ ጸሎታችን ከዕጣኑን መዓዛ ጋር የሚያርግባትን በደሙ የዋጃትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማወቅና መረዳት ይገባል። በተለይም በወጣትነት ዘመን በእግዚአብሔር ቃል ታንጾ ማደግ ያስፈልጋል። “በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን ዐስብ” (መክ. ፲፪፥፩) ሲል ጠቢቡ እንዳስተማረው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የገባችሁ ወጣቶች የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ከልጅነታችሁ ጀምሮ በሰንበት ትምህርት ቤት፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስትማሩ ያደጋችሁ ስለሆነ በተማራችሁበትና በተረዳችሁበት ልትጸኑ ይገባል።

በዚህም መሠረት በግቢ ጉባኤ የተሰበሰባችሁ ወንድሞችና እኅቶች የቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮዋ ሰፊና ተቀድቶ እንደ ማያልቅ ውቅያኖስ ውኃ ስለሆነ እንደ ጸጋ ስጦታችሁ በመማርና በማገልገል ራሳችሁን ልታበቁ፣ ከኃጢአትም ትጠበቁ ዘንድ ራሳችሁን ልታዘጋጁ ያስፈልጋል።

በአንዳንዶቹ ዘንድ በተለይም ከቤተሰብ መራቃቸውን እንደ ነፃነት በመቁጠር “ከዚህ በፊት የተማርነው ትምህርት ይበቃናል” የሚል አስተሳሰብ በመያዝ

መልእክት

ከእግዚአብሔር ቃል በመራቅ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ለመፈጸም ወዲህ ወዲያ የሚሉ እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን እናንተ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ለዘመኑ የተሳሳተ አስተምህሮ ሳትጋለጡ "አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህት ጸንተህ ኑር" በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ ለጢሞቴዎስ እንዳስተማረው በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ ልትጸኑ በዚህም መልካም የሆነውን ፍሬ ልታፈሩ ይጠበቅባችኋል፡፡ ወጣትነት የራሱ የሆኑ ፈተናዎች አሉትና ሊጥላችሁ የሚታገላችሁን ሥጋዊ አስተሳሰብና ፍላጎት በመግታት በጾምና በጸሎት ድል መንሣት ያስፈልጋል፡፡ ስለ ክርስትና ሃይማኖታችሁ በትክክል የተረዳችሁ፣ በመደበኛ ትምህርታችሁም የበረታችሁ ሁለገብ ሰዎች እና የወደፊት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለመሆንም መዘጋጀት ይጠበቅባችኋል፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ባላት መዋቅር ልጆቿን የማስተማር፣ የመንከባከብ ግዴታዋን ለመወጣት ለማኅበራችሁ ማኅበረ ቅዱሳን ሙሉ ዕውቅና እና ኃላፊነት መስጠቷ ይታወቃል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳንም እናንተን የግቢ ጉባኤ ተማሪዎችን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንድትማሩ ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ፣ መምህራንን መድቦ በማስተማር ላይ እንደሚገኝ ተገንዝባችሁ የዕድሉ ተጠቃሚዎች እንድትሆኑ፣ የድርሻችሁንም እንድትወጡ ይገባችኋል፡፡ ከዚያም አልፎ የአብነት ትምህርት ተምራችሁ የጸጋ ልጅነትን ሰጥታችሁ በክርስቶስ ክርስቲያንን ያሰኘቻችሁን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቤተ መቅደስ አገልግሎት በማገልገል የልጅነት ድርሻችሁን ትውጡ ዘንድ እንድትፋጡኑ ያስፈልጋል፡፡

በዚህም መሠረት በመደበኛ ትምህርታችሁ የቆይታ ጊዜ ማኅበረ ቅዱሳን በግቢ ጉባኤ የሚሰጠውን ተከታታይ ትምህርት፣ ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት የሚዘጋጁ ልዩ ልዩ መርሐ ግብሮችን እና የአብነት ትምህርት በአግባቡ ጊዜአችሁን አብቃቅታችሁ በመከታተል መንፈሳዊ ሕይወታችሁን አጠናክራችሁ ቀጥሉ እያልን መልእክታችንን እናስተላልፋለን፡፡

የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለየን፡፡ አሜን፡፡

‘‘እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት’’

(ማቴ. ፲፫፥፲፪)

በቀሲስ ኀይለሚካኤል ብርሃኑ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ የወይን ግንድ ስለመሆኑና አምነው የተከተሉት ሁሉ ደግሞ ቅርንጫፎች እንደሆኑ በብዙ ምሳሌ ካስረዳ በኋላ ከላይ በርዕስ የተነሣንበትን ቃል ተናግሯል፡፡ “እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ የእኔ ትእዛዜ ይህች ናት፣ ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ያለ እንደሆነ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለም፤ እናንተስ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ካደረጋችሁ ወዳጆቼ ናችሁ” (ዮሐ.፲፭፥፲፪-፲፭) ባለት ተናግሯል፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ እርስ በእርሳችን እንዋደድ ዘንድ እንደሚገባ ከማዘዙ አስቀድሞ እርሱ እኛን የወደደበትን ፍጹም ፍቅሩ አብነት እንዲሆነን ጠቅሶልናል፡፡ እርሱም ፍጹም አምላክ፣ ፍጹም ሰው ሆኖ በሥጋ የተመላለሰው እኛ የሰው ልጆች በግብራችን (በሥራችን) ደካሞች ብንሆንም በነገር ሁሉ ብርቱ የሆነውን እርሱን ተመልክተን ከድካማችን እንድንበረታ ነው፡፡

ለዚህም ነው ጌታችን በወንጌሉ “እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ፣ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ ነኝና በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና” (ማቴ. ፲፩፥፳፰) በማለት ያስተማረን፡፡

ስብከት

እኛ ምንም ሳይኖረን በበደላችን ምክንያት ከጸጋው ተራቁተን፣ በኃጢአት ተጎሳቁለን፣ ደስታ ርቆን በኀዘን ተውጠን ሳለ እንዲሁ የወደደን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከእኛ ምንም አገኛለሁ ወይም እጠቀማለሁ ሳይል ሕመማችንን የታመመ፣ ስለ እኛ የቆሰለ፣ ሞታችንን ሞቶ ሕይወቱን ያደለን እርሱ ፍቅር ስለሆነ ነው። እንግዲህ እንዲህ ያለ ዋጋ እንደ ወደደንና መተኪያ የሌለውን የደም(የሕይወት) ዋጋ ከፍሎልን ፍጹም ፍቅሩን እንዳሳየን ሁሉ እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ አዝዞናል።

እርሱ እንደወደደን እርስ በርሳችን መዋደድ ማለትም፡- ጥቅምን፣ ዋጋን፣ ክፍያን፣ ውለታን ምክንያት ሳናደርግ እንዲሁ ያለ ዋጋ፣ ያለ ውለታ፣ ያለ ጥቅም መዋደድ ነው። ይህም ያለው ለሌለው፣ ያገኘው ላላገኘው፣ የተማረው ላልተማረው፣ የበረታው ለደከመው ነገ ይከፍለኛል ወይም ውለታዬን ይመልስልኛል ብሎ ሳያስብ እንዲሁ ያለ ዋጋ በነፃ የሚደረግ ስጦታ ከእውነተኛ ፍቅር የተገኘ ነው።

እርስ በእርስ መዋደድ፡- ዘርን፣ ብሔርን፣ ቋንቋን ምክንያት ሳያደርግ ድሃ፣ ባለጠጋ ሳይል ሁሉን በእኩል ዓይን መመልከትና መውደድ ነው። አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ ከሰጠው ከዐሥሩ ትእዛዛት መካከልም አንዱ “ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ” (ዘሌ.፲፱፥፲፰) የሚል ነው።

ስለዚህ ክርስትና ስለ ራስ ብቻ የሚኖሩበት፣ ስለራስ ብቻ የሚያስቡበት፣ ስለራስ ብቻ የሚጨነቁበት ሕይወት ሳይሆን ስለ ሌላውም የሚኖሩት፣ የሚያስቡበት፣ የሚጨነቁበት፣ የመረዳዳትና የመተሳሰብ ሕይወት ነው። ለዚህም ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ “ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ኦሪትም ነቢያትም የሚያዝዙት ይህ ነውና” (ማቴ. ፯፥፲፪) እንዲል።

የክርስትና ሃይማኖት እርስ በእርስ የሚፋቀሩበት፣ የሚረዳዱበትና የሚተሳሰቡበት ሕይወት ነው። ለዚህ ደግሞ እንቅፋት የሚሆኑብንን ክፉ ምግባራት ከሕይወታችን ልናስወግዳቸው ይገባል። እነዚህ ክፉ ምግባራት ራስን ከመጉዳታቸው በተጨማሪ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ክርስቲያናዊ የሆነ መልካም ግንኙነት እንዳይኖረንና እውነተኛ ፍቅር እንዳናሳይ የሚያደርጉ ናቸው። በመሆኑም እነዚህን የመልካምነት እንቅፋቶች የሆኑትን፣

ከክርስቲያናዊ ሕይወት ሊወገዱ የሚገባቸውን ክፉ ተግባራት ከብዙው በጥቂቱ ስንመለከት፡-

፩ኛ . ራስ ወዳድነት

ራስ ወዳድነት ሲባል ስለ ራስ ምቾትና ጥቅም ሲባል ብቻ በጣም ከማሰብ የተነሣ ስለ ሌሎች ሰዎች ወይም ስለ ማኅበረሰቡ ግዴለሽ መሆንና እንዲያውም ስለ ግል ጥቅም ሲባል የሌላውን ሰው መብት መጋፋት ማለት ነው፡፡ ስለ ሌላው ሰው ማሰብ ሲባል ደግሞ ሰው ለራሱ እንዲሆንለት ወይም እንዲደረግለት የሚፈልገውን ጉዳይ ለሌላም ሰው እንዲደረግለት መመኘት ወይም ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በራስ ሊደርስ የማይፈለግ ድርጊት በሌላ ሰው ላይ እንዲደርስ አለመመኘት ነው፡፡

ይህንን በጎ ተግባርም የእምነት አባት አብርሃም በመፈጸሙ እንደ ምሳሌ ተጠቃሽ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነገረን አብርሃምና ሎጥ በቤቴል ሰፍረው ሳለ እግዚአብሔር በብዙ ባረካቸው እጅግ የብዙ መንጎች ባለቤትም ሆኑ ነገር ግን መንጎቻቸው ከመብዛታቸው የተነሣ የማሰማሪያ ስፍራ ስለ ጠበባቸው እረኞቻቸው መጋጨት ጀመሩ፡፡ በዚህን ጊዜ አብርሃም ሎጥን እኛ ወንድማማቾች ነንና በእኔና በአንተ፤ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ...አንተ ግራውን ብትወስድ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ አንተም ቀኙን ብትወስድ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ በማለት የመረጠውን ይወስድ ዘንድ የወንድሙን ምርጫ አስቀደመ፡፡

ምንም እንኳ አብርሃም በታላቅነቱ ቅድሚያና መከበር የሚገባው ቢሆንም እርሱ ግን ምርጫን ለወንድሙ ልጅ ለሎጥ ትቶለት ከራስ ወዳድነት ሸሸ፡፡ ሎጥ ግን በወቅቱ የራሱን ምርጫ በማስቀደም የተሻለ መስሎ የታየውን አቅጣጫ መረጠ፡፡ ከዚያ በኋላ ሎጥ የመረጠው ሀገር ሰዶምና ገሞራ እንዲጠፉ በተወሰነበት ጊዜ ከዚያች ተሰዶ ተንከራተተ፡፡ አብርሃምን ግን ባለበት ቦታ እግዚአብሔር ባረከው (ዘፍ. ፲፫፥፰)፡፡

ይህንን አስመልክቶ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በወንጌል "ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" በማለት አስተምሮናል (ሉቃ. ፮፥፴፩)፡፡

ብዙዎች መንፈሳውያን ሰዎችም ከራሳቸው ክብርና ጥቅም ይልቅ የሌላውን

ሰው ክብርና ጥቅም ያስቀድማሉ፡፡ በዚህ በጎ ተግባራቸውም እንደ አብርሃም ተባርከውበታል፡፡ በመሆኑም ለኔ ብቻ ይመቸኝ እንጂ ስለ ሌላው ምን ገዶኝ ከሚለው ራስ ወዳድነት ይልቅ ጸጋና በረከት የሚገኝበትን ለሌላ ሰው የማሰብን ጠባይ ቅዱሳን አባቶቻችን አብነት አድርገን ፈለጋቸውን እንከተል ዘንድ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ክርስትና ስለ ራስ ብቻ ሳይሆን ስለ ሌላውም የሚኖሩበት ሕይወት ነው፡፡ ነገር ግን በተቃራኒው ስለ ራስ ብቻ በማሰብ፣ እኔን ከተመቸኝ፣ ለእኔ ከሆነልኝ፣ እኔን ከተስማማኝ፣ ለእኔ ከዘነበለልኝ በማለት ግላዊ ጥቅምንና የራስን ድሎት ብቻ በማስቀደም የሚኖሩት ሕይወት መንፈሳዊ ሳይሆን ሥጋዊ (ዓለማዊ) ኑሮ ነው፡፡ ለዚህም የሚጠቀስ አንድ አባባል አለ፡፡ እሱም፡- “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ” የሚል ነው፡፡ ይህንን ቃል ራሱን ብቻ የሚወድ፣ ስለ ራሱ እንጂ ስለ ሌላው ምንም የማይገደው መሆኑንና ይህም ክፉ ጠባይ እንደሆነ ለማሳየት ነው፡፡

ራስ ወዳድ ሰው የራሱን ጥቅም ለማስከበር ሲል በወንድሙ ደም ይረማመዳል፤ ሌላውን ገፍትሮ ጥሎ ራሱ ብቻ ለመቆም ይጥራል፤ የሌላውን ዕድል ሰብሮ የራሱን ነገር ብቻ ያደላድላል፡፡ ይህ ደግሞ ከክርስቲያናዊ ሕይወት የማይጠበቅ እኩይ ተግባር ነው፡፡ ከቅዱሳን አባቶቻችን ሕይወት እንደተማርነው ክርስትና እየተራቡ ሌላውን ማብላት፣ እየሞቱ ሌላውን ማዳን፣ እየተቸገሩ ሌላውን ከችግሩ ማውጣት፣ ራስን ዝቅ አድርጎ ሌላውን ማክበር፣ … ወዘተ እንደሆነ እናስተውላለን፡፡

፪ኛ. ስስታምነት

ስስታምነት ባለን ነገር አለመርካት፣ ተመስገን አለማለት፣ ያለንን ነገር ሳይሆን ሁል ጊዜ የለኝም የምንለውን ነገር ማሰብ፣ ያለንን ብዙ ነገር ባለማስተዋል የሌለንን ጥቂት ነገር ባለማግኘታችን በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ማጉረምረም ነው፡፡ አንድ ሰው በፊቱ ያለውን ሳያነሣ የጀርባውን የሚመኝ፣ የቆረሰውን ሳይጎርስ በሚመገበው ላይ ዓይኑን የሚጥል፣ የቀረበለትን ሳይበላ ነገ ስለሚቀርበለት የሚጨነቅ፣ የራሱ እያለው የሌላውን የሚመኝ ከሆነ ስስታም ይባላል፡፡

ስስት ለማኅበራዊ ኑሮም ሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወት እንቅፋት ነው፡፡

ምክንያቱም ስስታም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የለውም፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ “በዓይኑ ትዕቢተኛ የሆነውና ልቡ የሚሳሳው ከእኔ ጋር አይተባበርም” (መዝ. ፩፻፩፥፭) ይላልና፡፡

ስስታምነት የሚመጣው ከሆዳምነት ወይም ከአልጠግብ ባይነት ነው፡፡ በመሆኑም መቀበል እንጂ መስጠት፣ መለመን እንጂ መለመን (እባክህ መባል) የማይወድ ሰው ስስታም ይባላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው ቢበላም አይጠግብም፣ ቢጠጣም አይረካም፣ ቢለብስም አይሞቀውም፡፡ ምክንያቱም ስስት አንቆ ይዞታልና በጥቂትም ሆነ በብዙው ነገር መርካት አይችልም፡፡

ክርስቲያናዊ ሕይወት ግን ከእንዲህ ዓይነት ነገር የራቀ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጁ ጢሞቴዎስን ሲመክር “በቃኝ ከማለት ጋር እግዚአብሔርን ማምለክ ታላቅ ረብ ነው፡፡ ወደ ዓለም ያመጣነው የለንምና ከእርሱም ልንወስደው የምንችል የለንም፡፡ ምግባችንን እና ልብሳችንን ካገኘን ይበቃናል፡፡ ባለጸጋ ሊሆኑ የሚወዱ ግን በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያስንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ” (፩ኛ ጢሞ. ፮፥፮) ብሏል፡፡

፫ኛ. ክፉ ቅንዓት

ክፉ ቅንዓት ለክርስቲያናዊ ሕይወት ጠንቅ ነው፡፡ ይህም በሌላው ማግኘት፣ መክበር፣ መበልጸግ፣ ማደግና ወደተሻለ ነገር መሸጋገር መናደድ ለምን እገሌ ተለወጠ? ለምን እገሊት ከፍ አለች? በሚል የክፋት አሳብ መያዝ ነው፡፡ ክፉ ቅንዓት በራስ ሳይሆን በሌላ ማግኘት መበሳጨት ነው፡፡ ምንም እንኳ ያ በክፉ ቅንዓት የተያዘ ሰው የማያገኘው ወይም የማይደርስበት ነገር ቢሆንም እንኳ ሌላው ሰው (አካል)እንዳያገኘው ወይም እንዳይደርስበት መፈለግ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ክፉ ጠባይ ለማኅበራዊ ኑሮም ሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወት እንቅፋት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ክፉ ቅንዓት ቃዔል በወንድሙ በአቤል ላይ እንደቀናበት ያለ ቅንዓት ነው፡፡ እንደምንመለከተው በዚህ ክፉ ቅንዓት ሰበብ ብዙ ወንድማማቾች ተለያይተዋል፣ ወዳጆች ወዳጅነታቸውን ሰርዘውበታልና ከክፉ ቅንዓት መራቅ ያስፈልጋል፡፡

፬ኛ. ዘረኝነት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝብና አሕዛብ የታረቁበት የሰላም ባለቤት ነው። ለሰው ልጅ ሕይወት እውነተኛ ሰላም ያደለው እርሱ ነው። ይህንን ያልተረዱ አንዳንድ ግለሰቦች ግን ዛሬም ድረስ የሀገሬ ልጅ፣ የወንዜ ልጅ እየተባባሉ ራሳቸውንም ሆነ ሌላውን የሚጎዱ ጥቂት የሚባሉ አይደሉም። የክርስትና ሃይማኖት የፀብ ግድግዳ የፈረሰበት ሁሉን በእምነት አንድ ወገን ያደረገ ሃይማኖት መሆኑን ያልተረዱ በየስፍራው አይታጡም። ዘረኝነትን ከውስጣችን ካላጠፋን ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ መገለጥ አይችልም። ምክንያቱም ዘረኝነት አንዱ ለክርስቲያናዊ ሕይወት እንቅፋት ስለሆነ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ሰዓት እየተፈተነች ያለችበት አንዱ የዘረኝነት ጉዳይ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የሥጋ ሥራ ብሎ ከዘረዘራቸው መካከል አንዱ ይኸው ዘረኝነት ነው። “ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና እርሱም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ” የሚል ነው። ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱ ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ” (ገላ. ፭፥፲፬) እንዲል። በመሆኑም ዘረኝነትን ከመካከላችን አስወግደን እውነተኛ ፍቅርን ገንዘብ ማድረግ ለማኅበራዊ ኑሮአችን አስፈላጊ ነው።

፭ኛ. ሐሜት

ሐሜት፡- ስለ አንድ ሰው እርሱ በሌለበት የነቀፋ ወይም የስም ማጥፋት ወሬ መናገር ነው። ሐሜት በእውነት ወይም በሐሰት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል። በእውነት ላይ የተመሠረተ በሚሆንበት ጊዜ የሚታማው ሰው የፈጸመውን ክፉ ድርጊት በማንሣት ባለቤቱም ሆነ ሌላው ሰው እንዲማርበት ተብሎ ሳይሆን በድክመቱ ሌላው ሰው እንዲዘባበትበት በማሰብ ሆን ተብሎ ለሌላው ወገን በነቀፋ መልክ መናገር ነው።

ሐሜት በሐሰት ላይ የተመሠረተ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” እንደሚባለው ሁሉ ሆን ተብሎ የሰው ስም ለማጥፋት ወይም ለመጉዳት ሲባል የሚወራ ክፉ ወሬ ግን እርስ በርስ በመዋደድ ፍቅርን የሚያደርግ ሰው ከሐሜት ይርቃል። በመሆኑም ክርስቲያናዊ ሕይወት

ያለው ሰው ምንም እንኳ በዙሪያው ያሉ ሰዎች ኢ-ክርስቲያናዊ ተግባር የሆነውን የሐሜትን ቃል ቢናገሩም ሰምቶ እንዳልሰማ ዝም ይላል እንጂ ከእነሱ ጋር ለሐሜት አይተባበርም፡፡

ሐሜት በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ተግባር ከመሆኑ ባሻገር ለማኅበራዊ ኑሮ ጠንቅ ነው፡፡ በክርስቲያናዊ ሕይወትም አይፈቀድም፡፡ ለዚህ ነው ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ “እግዚአብሔር ሆይ ወደ መኖሪያህ መግባት የሚችል ማነው? የሌሎች ሰዎችን ስም የማያጠፋ… ጎረቤቶቹን የማያማ… እነዚህን ነገሮች የሚያደርግ ሰው ከማናቸውም ክፉ ነገር ተጠብቆ ይኖራል እንጂ ከቶ አይናወጥም” (መዝ. ፲፭፥፩) በማለት ስለ ሐሜት ነውርነት አስገንዝቧል፡፡

ከላይ የዘረዘርናቸው ነጥቦች ፍቅርን የሚያቀዘቅዙ፣ እርስ በእርስ መዋደድን፣ መተሳሰብን የሚያርቁ በመሆናቸው ከልባችን ልናስወግዳቸው ይገባል፡፡

ከሁሉ ጋር በፍቅር መኖርን ገንዘብ ማድረግ ከክርስቲያን ይጠበቃል፡፡ “ፍቅር ያስታግሣል፣ ፍቅር ያስተዛዝናል፣ ፍቅር አያቀናናም፣ ፍቅር አያስመካም፣ ፍቅር ልቡናን አያስታብይም፡፡ …” በማለት ሐዋርያው እንደገለጸው ከሁሉም ጋር በወንድማማች መዋደድ መኖር ይገባል፡፡ (፩ቆሮ. ፲፫፥፬) በፍቅር የተገነባ ማንነት መልካም ቤተሰብን፣ ማኅበረሰብንና ሀገርን ለመገንባት መሠረት ነውና፡፡ ለዚህ ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት” በማለት ያስተማረን፡፡ (ማቴ. ፲፭፥፲፪) እግዚአብሔር አምላካችን እርስ በእርሳችን የምንግባባበትን እውነተኛ ፍቅር ለሁላችንም ያድለን አሜን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

“ብዙዎች አሳቾች ወደ ዓለም መጥተዋል”

(፪ዮሐ. ፩፥፯)

በመ/ር ቢትወደድ ወርቁ

ቤተ ክርስቲያን ከምታስተምረው መሠረታዊ ትምህርት አንዱ የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆንን ነው። ይህም የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ነው። በምሥጢረ ሥጋዌ ከሚነሣው ዋና ሐሳብ አንዱ የአካላዊ ቃል በሥጋ መገለጥ ነው። ቤተ ክርስቲያን የአካላዊ ቃልን ሰው መሆን የትምህርቷ አካል አድርጋ የምታስተምር ሲሆን የማያምኑና የሚያስክዱ አሉና ቅዱስ ዮሐንስ “ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም መጥተዋልና፤ ይህም አሳቹ ሐሳዊ መሲሕ ነው።” በማለት ይገልጻቸዋል። (፪ዮሐ. ፩፥፯) ይህን የተናገረውን ቃል መሠረት አድርገን የአሳቾችን መገለጫ በጥቂቱ እንመልከታለን፡-

፩. እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆኑን ይክዳሉ

ከድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት እግዚአብሔር ነው። ይህም የአባቶቻችን ቅዱሳን ነቢያት፣ ሐዋርያትና ቀደምት ሊቃውንት ምስክርነት ነው። ቅዱሳን ነቢያት ወልደ እግዚአብሔር በሥጋ ተገልጦ የሚፈጽማቸውን የማዳኑን ሥራዎች ሲናገሩ እግዚአብሔር መሆኑን መስክረዋል። ለምሳሌም፦

፩.፩. ስለ ልደቱ፡- ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ልደቱ ሲናገር “ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ፥ የዘለዓለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።” (ኢሳ ፱፥፮) እንዲል፤ ነቢዩ ኤርምያስ ደግሞ “እነሆ ለዳዊት የጽድቅ ቁጥቋጥ

የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፥ ንጉሥ ይነግሣል፥ ያስባል፣ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል።” (ኤር ፳፫፥፭) በማለት የወልደ እግዚአብሔርን መምጣት ይናገራል።

፩.፪. ስለ ትንሣኤው፡- ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት በተለያዩ የመዝሙራት ክፍሎቹ “እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፡ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያልም ሰው፤ ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ፤ የዘለዓለምን ኀሣር ሰጣቸው።” (መዝ ፸፯፥፷፭)፤ እንዲሁም፦ “እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶቹም ይበተኑ፥ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሽሹ።” (መዝ. ፷፯፥፩) በማለት በትንቢት መነጽር ተመልክቶ ቀድሞ ተናግሯል።

፩.፫. ስለ ዕርገቱ፡- ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት “አምላክ በእልልታ፣ እግዚአብሔር በመለከት ድምጽ ዐረገ። ዘምሩ፥ ለአምላካችን ዘምሩ፥ ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ።” (መዝ. ፵፮፥፭) በማለት ሲገልጽ ዳግመኛም “በምሥራቅ በኵል ወደ ሰማየ ሰማያት ለወጣ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ የኃይል ቃል የሆነ ቃሉን፥ እነሆ ይሰጣል። ለእግዚአብሔር ክብር ስጡ፤ ግርማው በእስራኤል ላይ ኃይሉም በደመናት ላይ ነው።” (መዝ. ፷፯፥፴፫) ብሏል።

፩.፬. ስለ ዳግም ምጽአቱ፡- በዓለም ፍጻሜ በግርማ መለኮት በክበበ ትስብእት ተገልጦ፥ ለጻድቃን የሚፈርድላቸው፤ በኃጥኣን የሚፈርድባቸው ዓለምንም ከመኖር ወደ አለመኖር የሚያሳልፉት ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ የከበረ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ነው። (ማቴ. ፳፬፥፴፤ ፳፭፥፴፩፤ ፩ተሰ.፬፥፲፮፤ ራእ.፳፪፥፲፪)

ቅዱስ ዳዊት “ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል። አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም፤ እሳት በፊቱ ይቃጠላል፥ በዙሪያው ብዙ ዐውሎ አለ። በላይ ያለውን ሰማይን፣ ምድርንም በሕዝቡ ለመፍረድ ይጠራል።” (መዝ. ፵፱፥፪፤ ፪ተሰ. ፩፥፯-፰) እንዳለው።

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስም “እነሆ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል፤ ክንዱም ስለ እርሱ ይገዛል። እነሆ፥ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም

በፊቱ ነው።" (ኢሳ. ፵÷፲፤ ራእ. ፳፪÷፲፪) ነቢዩ ዘካርያስ "አምላኬ እግዚአብሔር ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ይመጣል።" (ዘካ. ፲፬÷፭-፯፤ ማቴ፳፭÷፴፩) እንዲል።

ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በእኛ አደረ

ቃል የተባለው አካላዊ ቃል፣ ቃለ አብ፣ ቃለ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ መሆኑንና እርሱም ከቀድሞውም በአምላክነቱ ክብር እንደ ነበር ወንጌላዊው ሲገልጽ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።" ብሏል። ፈጣሪነቱንም "ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ያለ እርሱ አልሆነም" በማለት መስክሯል። (ዮሐ ፩÷፩-፫) ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ስለ አካላዊ ቃል ይህን ከተናገረ በኋላ "በቅድምና ነበረ፤ እግዚአብሔር ነበረ፤ ሁሉ የሆነው በእርሱ ነው ያልኳችሁ ቃል ሥጋ ሆነ" ብሎ ሰው መሆኑን ገለጠልን። "ቃል ሥጋ ሆነ" የሚለውን የሐዋርያውን ቃል በጥንቃቄ ካልተረዳነው እንስታለን።

መናፍቁ አቡሊናርዮስና ተከታዮቹ "ቃል ሥጋ ሆነ" የሚለውን ባለመረዳታቸው "አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን እንጂ ነፍስን አልነሣም" ብለው ክደዋል። "ቅዱሳት መጻሕፍትን በነጠላ ትርጓሜ መተርጎምና መረዳት እንችላለን።" ይሉ የነበሩ የአንጾኪያ ትርጓሜ ትምህርት ቤት መናፍቃን "ሆነ" የሚለውን ይዘው በራሳቸው መረዳት ተታልለው "ቃል ሥጋ ሆነ ማለት፦ ቃል ወደ ሥጋነት ተለወጠ ማለት ነው" ብለው ስተው ሌሎችንም አስተዋል።

ቅዱስ ቄርሎስ "ቃል ሥጋ ሆነ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ ተርጉሞ አስተምሮናል። ቅዱስ ቄርሎስ "ቃል ሥጋ ሆነ ማለት ቃል ሰው ሆነ ማለት ነው።" ይልና ምክንያቱን ሲያስረዳ "በቅዱሳት መጻሕፍት ሰው ለማለት ሥጋ ወይም ነፍስ ማለት ልማድ ነው።" ይላል መናፍቃኑ ልብ ገዝተው ከስሕተታቸው ቢመለሱ በማለትም ከቅዱሳት መጻሕፍት ኃይለ ቃላትን ይጠቅስላቸዋል። ለምሳሌ፦ (ዘፀ.፩÷፭፤ መዝ.፷፫÷፩፤ ዮሐ.፫÷፵፬፤ ፲፪÷፳፯፤ ሉቃ.፳፫÷፵፮፤ ራእ.፳፪÷፲፭)

ሁለተኛ ቅዱስ ቄርሎስ ትኵረት የሰጠው "ኮነ፤ ሆነ" ለሚለው ቃል ነው። ቅዱስ ቄርሎስ "ቃልም ሥጋ ሆነ ማለት ቃል ተለውጦ ሥጋ ሆነ፥ ሥጋም ወደ አምላክነት ተለወጠ ማለት አይደለም። ነገር ግን በማይመረመር የተዋሕዶ ምሥጢር የቃል ገንዘብ ለሥጋ፤ የሥጋም ገንዘብ ለቃል ሆነ እንጂ" በማለት ያብራራል። ሊቁ እንዳስተማረው ማንም "ሆነ" የሚለውን ይዞ "ተለወጠ" እንዳይል ወንጌላዊው አስከትሎ "ጸጋንና እውነትን ይዞ በእኛ አደረ፤ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።" (ዮሐ ፩፥፲፬) በማለት ተናገረ።

"ኅደረ ወይም አደረ" ያለውንም ቃል ይዘው "ኅድረት" የሚል ክሕደት እንዳያመጡም "ሆነ" ብሎባቸዋል። ስለዚህም "ሆነ" እና "አደረ" የሚሉት ቃላት እንደ አለቃና ጠበቃ ተጠባብቀው "ተዋሐደ (አንድ ሆነ)" ተብለው ይተረጐማሉ። (ኤፌ ፪፥፲፬) ስለሆነም ቅዱስ ዮሐንስ "አንድ ልጅም (ወልድ ዋሕድ) ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን" አለን።

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ እነዚህን አሳቾች (መናፍቁ አቡሊናርዮስና ተከታዮቹ) "ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ ናቸው።" በማለት ሥጋ (ትስብእት) በተዋሕዶ ከብሮ ፍጹም የባሕርይ አምላክ መሆኑን የማያምኑ መሆናቸውን ገለጠልን። "ቃል ሥጋ በሆነ ጊዜ ነፍስን አልነሣም" ማለት ሊቁ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ እንዳስተማረው "የሰው ልጅ አልዳነም" ማለት ነው። ምክንያቱም ሰው ሥጋ ብቻ ሳይሆን ነፍስም ጭምር ነውና። ዓለምን የሚያድነው አዳኙ፦

ሀ. ሰው የሆነ፦ ለምን ቢሉ የበደለ፤ የተፈረደበትም ሰው ነው። ስለሆነም አዳኙም ሰው ካልሆነ ማዳኑና የተከፈለው ዋጋ የታወቀ አይሆንም። "ያም ቃል ሥጋ ሆነ፤ በእኛም አደረ፣ ለአባቱ አንድ እንደሆነ ልጅ ክብር ያለ ክብሩን አየን" (ዮሐ. ፩፥፲፬) በማለት እንደነገረን።

ለ. የሚሞት፦ በበደለው ሰው ላይ የተፈረደበት ቅጣት ሞት ነው። "ከእርስዋ በበላህ ቀን የሞትን ሞት ትሞታለህ።" ብሎ ለአዳም እንደተናገረው የተፈረደበትን የሞት ፍርድ አዳም ማስወገድ ስለማይችል አዳኙ (ኢየሱስ ክርስቶስ) የሞት ዕዳውን መክፍል ነበረበትና። (ዘፍ. ፪፥፲፯፣ ሮሜ. ፭፥፲፪)

ሐ. ሞትን የሚያሸንፍ፡- ሰውን የሚያድነው መድኃኒት መሞት ብቻ ሳይሆን ሞትንም የሚያሸንፍ ነው፡፡ "ይህ የሚፈርሰው የማይፈርሰውን በለበሰ ጊዜ፤ የሚሞተውም የማይሞተውን በለበሰ ጊዜ ሞት በመሸነፍ ተዋጠ፡፡" ተብሎ ተጽፏል፡፡ (፩ቆሮ. ፲፭፥፶፫-፶፬)

መ. ንጹሐ ባሕርይ የሆነ፡- ሰውን የሚያድነው አዳኝ ንጹሕ ካልሆነ ለሌሎች ቤዛ ሊሆን አይችልም፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሁኔታዎችን ማሟላት የሚችለው ሰው ነው። ምክንያቱም አምላክ በባሕርዩ ሞት አይስማማውም። በሦስተኛና አራተኛ የተጠቀሱትን የሚያሟላው ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በሞት ላይ ሥልጣን ያለው፤ ንጹሐ ባሕርይ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ተዋሕዶ ሰው ሆኖ፤ በሞቱ ሞትን አጥፍቶልን ቤዛ ሆነን፡፡ (ዮሐ. ፫፥፴፮፣ ዕብ. ፪፥፲፬-፲፮፣ ኤፌ. ፪፥፲)

፪. ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም የነበረ መሆኑን ይክዳሉ

እርሱ በሥጋ ከመገለጡ አስቀድሞ በመለኮታዊ ክብሩ ነበረ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊም በመልእክቱ ሊያስተላልፍልን የፈለገው የመጀመሪያው ጉዳይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከመፈጠሩ፣ ዘመን ከመቆጠሩ አስቀድሞ በመለኮታዊ ክብሩ የነበረ አምላክ መሆኑን ነው፡፡ ጌታችን ለድኅነተ ዓለም በአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ፍጻሜ በሥጋ መገለጡን (ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ መሆኑን) አስረዳን፡፡

በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ፎጢኖስ "ለፌ እማርያም ለወልድ ክዋኔሁ፤ የወልድ ህልውና የተጀመረው ከማርያም በተወለደ ጊዜ ነው፡፡" ብሎ እንደተናገረው ሳይሆን እርሱ "በዚህ ዘመን አልነበረም" የማይባልለት የዘመናት ባለቤት፤ አልፋና ዖሜጋ፤ ፊተኛውና ኋለኛው፤ መጀመሪያውና መጨረሻው መሆኑን ቅዱሳን ነቢያትና ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው የመሰከሩለት፡- ያለ ትናንት ቀዳማዊ፤ ያለ ዛሬ ማእከላዊ፣ ያለ ነገ ደኃራዊ፣ ዓለምንም አሳልፎ ለዘለዓለም የሚኖር ዘለዓለማዊ ነው፡፡

አካላዊ ቃል ሥጋ (አምላክ ሰው) በሆነ ጊዜም ዘመን የሚቆጠርለት ትስብእት በተዋሕዶ የመለኮትን ገንዘብ (ዘለዓለማዊነትን) ገንዘብ በማድረጉ ምክንያት

ጥንታዊ፣ ቀዳማዊ ሆኗልና “እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ” ብሎ ተናገረ። (ዮሐ ፰፥፶፰) “አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ” ያለው በሥጋ በተዋሕዶ የመለኮትን ዘለዓለማዊነት ገንዘብ በማድረጉ ምክንያት መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

በሥጋ ልደት ስድስት ወራት የሚቀድመው መጥምቁ ዮሐንስ “አንተ ማነህ? ኤልያስ ነህን? ነቢዩ ነህን?” ብለው በጠየቁት ጊዜ “አይደለሁም” አላቸው። እነርሱም መልሰው “እንኪያስ ክርስቶስን ካልሆንህ፣ ወይም ኤልያስን፣ ነቢይም ካልሆንህ ለምን ታጠምቃለህ?“ ብለው በጠየቁት ጊዜ መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ “እኔ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፣ ነገር ግን እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል፣ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት የነበረው የጫማውን ጠፍር ልፈታ እንኳ የማይገባኝ ነው” አላቸው። (ዮሐ.፩፥፳፬-፳፰)

በነገውም ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ “...አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል፥ ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል፤ ብዬ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው።” (ዮሐ ፩፥፲፱-፴) ብሎ የመሰከረው የጌታችንን በቅድምና መኖር የሚመሰክር ትምህርት ነው። መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ እየመሰከረ ያለው ስለ አንድ ክርስቶስ (ወልድ ዋሕድ) መሆኑን ልብ እንበል።

“አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል” ሲል መጥምቁ ዮሐንስ ጌታችንን በሥጋ ልደት በስድስት ወራት እንደሚቀድመው የሚያስረዳ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ በሥጋ ልደት ቢቀድመውም ትስብእት ከመለኮት ጋር ተዋሕዶ የመለኮትን ገንዘብ (ዘለዓለማዊነትን በቅድምና መኖርን) ገንዘቡ አድርጓልና “ከእኔ በፊት ነበርና” ብሎ መሰከረለት። በዚህም ዘመን የማይቆጠርለት መለኮት በተዋሕዶ ዘመን ተቆጠረለት፤ ዘመን የሚቆጠርለት ትስብእትም ዘመን የማይቆጠርለት ቀዳማዊ መሆኑን ተረዳን።

በፍጥሞ ደሴት ለወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በመደጋገም “አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ፥ እነሆም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ።” (ራእ. ፩፥፲፯-፲፱) እንዲሁም “አልፋና ዖሜጋ

ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ፡፡" (ራእ. ፳፪፥፲፪) በማለት የተናገረው ማን ነው? ከመለኮት ጋር በተዋሕዶ የከበረ ትስብእት አይደለምን? ሥጋ በተዋሕዶ ከብሮ የመለኮትን ገንዘብ፤ ገንዘቡ ባያደርግ "ፊተኛውና ኋለኛው እኔ ነኝ፡፡" ብሎ ባልተናገረ ነበር፡፡ ፊተኛነት፣ ኋለኛነት የመለኮት ባሕርያዊ ገንዘቦቹ ናቸውና፡፡

አምላክ ሰው ሲሆን ሰውነት በተዋሕዶ ለመክበሩ ሌላው ማሳያ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ "አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ፡፡" (ዮሐ ፲፯፥፭) ብሎ መናገሩ ነው፡፡ ዓለም ሳይፈጠር (ቅድመ ዓለም) ሰውነት አልነበረም፡፡ በአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ፍጻሜ ቃል ሥጋ በሆነ ጊዜ ግን ሥጋ በተዋሕዶ የመለኮትን ቅድምና ገንዘቡ በማድረጉ "ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ" በማለት ተናገረ፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ የ"ቃል ሥጋ ኮነ"ን ትምህርት ባስተማረበት የወንጌል ክፍል "ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን፡፡" (ዮሐ ፩፥፲፬) በማለት የገለጠውም የአምላክ ሰው መሆን በፍጹም ተዋሕዶ መሆኑን በእውነት ያስረዳል፡፡

፫. የባሕርይ አምላክ መሆኑን ይክዳሉ

ወልደ አብ ወልደ ማርያም ሥግው ቃል ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጥረታትን ያለ ድካም የፈጠረ ፈጣሪ ነው፡፡ (ኤፌ. ፪፥፲፤ ዮሐ. ፩፥፫፤ ቆላ. ፩፥፲፭-፲፯) አምላክነቱም እንደ ቅዱሳን የጸጋ፣ እንደ ሰይጣንና ጣዖታትም የሐሰት አይደለም፡፡ (መዝ. ፹፩፥፱፤ ዮሐ. ፲፥፴፬፣ ዘጸ. ፯፥፩) እርሱ አምላክነቱ የባሕርዩ ነው፡፡ ይህም የቅዱሳን ነቢያትና ሐዋርያት ምስክርነት እንደ ነበር የሚከተሉትን ኃይለ ቃላት በመመልከት መገንዘብ ይገባል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ "እኛስ ሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ አንተ እንደሆንህ አምነናል፣ አውቀናልም" በማለት ገልጾታል፡፡ ቅዱስ ዳዊት ስለ ዕርገቱ ሲመሰክርም "አምላክ በእልልታ፣ እግዚአብሔር በመለከት ድምጽ ዐረገ፡፡ ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ፥ ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ፡፡" በማለት የባሕርይ

አምላክነቱን መስክሯል፡፡ (መዝ ፵፬፥፮፣ ሉቃ ፳፬፥፶-፶፩፣ ዮሐ. ፮፥፳፱፤ የሐዋ ፩፥፲፩)

ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱም "ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው፡፡" (ሮሜ. ፱፥፭) ሲል ይመሠክራል፡፡ እንዲሁም ወደ ደቀ መዝሙሩ ቲቶ በላከው መልእክት "የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁን ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፡፡" (ቲቶ ፪፥፲፫) ይላል፡፡

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም የባሕርይ አምላክነቱን ሲገልጽ "የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው፡፡" (፩ዮሐ. ፭፥፳) በማለት የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነትን መስክረዋል፡፡

ነገር ግን ዲያብሎስና የግብር ልጆቹ የእግዚአብሔር ወልድን በሥጋ መገለጥና የባሕርይ አምላክነት በመካድ ብዙዎችን በማሳት ከመንግሥተ እግዚአብሔር ለመለየት ይጥራሉ፡፡ እኛ ግን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" እንዳለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ተዋሕዶ ወደዚህ ምድር ለድኅነተ ዓለም እንደመጣ፣ እንደ ተሰቀለ፣ እንደ ሞተ፣ በሦስተኛውም ቀን ሞትን ድል አድርጎ እንደ ተነሣ፣ በአርባኛውም ቀን እንደ ዐረገ፣ ዳግም ይህንን ዓለም ለማሳለፍ እንደሚመጣ እናምናለን፡፡ የአመነውም የስሙ ቀዳሾች፣ የክብሩ ወራሾች ያደርገን ዘንድ በቸርነቱ ይርዳን፤ አሜን፡፡

“በግቢ ጉባኤ ውስጥ መሳተፍ ቤተ ክርስቲያንና ሀገርን ለማገልገል መሠረት የምንጥልበት ጊዜ ነው”

(ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን)

በእንዳለ ደምስስ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ኦርቶዶክሳውያን የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ዘንድ መንፈሳዊ ሕይወታቸውንና መደበኛ ትምህርታቸውን አቀናጅተው ለመማር በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ አንዳንድ ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ችግሮች ያጋጥማቸዋል፡፡ እነዚህንም ችግሮች ተቋቁመው ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የዋንጫና የሜዳልያ ተሸላሚዎች ሆነው የሚመረቁ ብዙዎች ቢሆኑም አንዳንድ ተማሪዎች ግን በትምህርታቸው ሲቸገሩ እንመለከታለን፡፡ ከዚህም በመነሣት “እንዴት ውጤታማ መሆን እችላለሁ?” እያሉ የሚጨነቁ ወንድሞችና እኅቶች ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ወደ ዝግጅት ክፍላችን ይልካሉ፡፡ እኛም ጥያቄአቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ምላሽ ይሰጡን ዘንድ ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን የሐመር መጽሔት ምክትል ዋና አዘጋጅን ጋብዘናል፡፡ እነሆ፡፡

ጉባኤ ቃና፡- በግቢ ጉባኤያት የሚሳተፉ ተማሪዎች ብዙዎቹ “በመንፈሳዊ እና በመደበኛ ትምህርቴ ውጤታማ እሆን ዘንድ ምን ላድርግ?” በማለት

በተደጋጋሚ ይጠይቃሉ፡፡ እርስዎም በግቢ ጉባኤያት ውስጥ እንደማለፍዎ ከተሞክሮዎ በመነሣት ምላሽ ቢሰጡን?

ቀሲስ ዐቢይ፡- በመጀመሪያ ዓለማዊውና መንፈሳዊው ትምህርት ለሰው ልጆች ሁሉ ተገቢና አስፈላጊ እንደሆኑ መረዳት ይገባል፡፡ ሁለቱም ሕይወታችን ጠቃሚ ናቸውና፡፡ ዓለማዊውን ትምህርት ለመማር ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ሲገቡ ለዋናው(መደበኛው) ትምህርት ትኩረት በመንፈግ ወደ መንፈሳዊው ትምህርት ብቻ በማድላት ውጤት ሲርቃቸው እግዚአብሔርን የሚያማርሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በመደበኛው ትምህርቴ ውጤታማ እንዳልሆን፣ የጥናት ጊዜዬን ስለሚሻማብኝ መንፈሳዊ ትምህርቱን አልማርም በማለት የሚሸሹም አሉ፡፡

ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሲገቡ በዋነኛነት በመደበኛ ትምህርታቸው ውጤታማ ሆነው እንዲወጡ ሲሆን በቆይታቸውም ዓለማዊውን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊውንም ሕይወታቸው እንዲያዳብሩ፣ በሃይማኖት ጸንተው፣ ራሳቸውንም ከኃጢአት ጠብቀው ለውጤት እንዲበቁ ለማስቻል ማኅበረ ቅዱሳን ላለፉት ሠላሳ አንድ ዓመታት አገልግሎቱን ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በዚህ አገልግሎት ውስጥ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ዓላማቸውን ሳይዘነጉ ራሳቸውንም በዕቅድ በመምራት ለትምህርታቸው፣ ለጥናት፣ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸውና ለአገልግሎት፣ እንዲሁም ለዕረፍታቸው ሰዓት በመመደብ ሁሉንም አመጣጥነው ውጤት ይዘው እንዲወጡ መንገዱን ማሳየት ነው፡፡

ነገር ግን ከመደበኛው ትምህርታቸው ይልቅ ለመንፈሳዊው ሕይወታቸው ከፍተኛውን ጊዜ በመስጠት ጊዜያቸውን ሲያባክኑ ማየት የተለመደ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ለመደበኛ ትምህርታቸው ትኩረት በመንፈግ በመጨረሻም ውጤታማ ሳይሆኑ ባክነው ይቀራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን እያገለገልኩ፣ ረጅሙን ጊዜዬን ለመንፈሳዊ ሕይወቴ ሰጥቼ እግዚአብሔር እንዴት አሳልፎ ይሰጠኛል በማለት እግዚአብሔርን ተወቃሽ ያደርጉታል፡፡ ለምን ሰንበት ትምህርት ቤት እየሄድሁ፤ ግቢ ጉባኤ እየተማርሁ፤ ወደ ገዳማት፣ ወደ ጸበል እየተመላለስሁ በትምህርቴ ደከምኩ ማለትን ያበዛሉ፡፡ ነገር ግን ሁለቱም እንደሚያስፈልጉ መረዳት ተገቢ ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላካችን ሲፈጥረን ሥጋዊ ፍላጎት ያለን ሥጋውያን፣ መንፈሳዊ ፍላጎት

ያለን መንፈሳዊያን አድርጎናል፡፡ ስለዚህ ሳይንሱም ሆነ መንፈሳዊው ሕይወት ስለሚስፈልገን ሁለቱንም አጣጥመን መሄድ የእኛ ድርሻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን አስተምሮ ልጆች ከተግባረ ሥጋ፣ ከተግባረ ነፍስ አስቀድሞ ትምህርተ ሃይማኖትን፣ አእማደ ምሥጢራትን ሊያስተምሯቸው ይገባል፡፡ ተግባረ ነፍስ ስንል፡- መጾም፣ መጸለይ፣ መስገድ፣ መመጽወት፣ … የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ ተግባረ ሥጋ ደግሞ ማረስ፣ መቆፈር፣ መጻፍ፣ መደጎስ፣ ሥጋዊ ትምህርት መማር የምንለው ነው፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ አስቀድሞ ትምህርተ ሃይማኖትን ማለትም ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ፣ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ምሥጢረ ቁርባንና ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን (አምስቱ አእማደ ምሥጢራት) መማር ይገባል፡፡

አሁን አሁን የዚህ ቅደም ተከተል ተዛብቶብናል፡፡ በከተማ ከመንፈሳዊው ይልቅ ቀድሞ ሳይንሱ ነው የሚነገረው፣ በገጠሩም የትምህርት ዕድል የማያገኘውም ቢሆን ቀድሞ ስለ ማረሱ ስለ መቆፈሩ እንጂ ስለ ሃይማኖቱ አይነገረውም፡፡ ይህ አካሄዳችን ደግሞ ብዙ ነገሮቻችን ማለትም ማኅበራዊ፣ ኢኮኖማዊ ፣ ፖለቲካዊ፣ ሀገራዊ ቀውስ ፈጥሯል፡፡ ይህ የቅደም ተከተል መዛባት የልጆች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የወላጆችም ጭምር ስለሆነ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ ወላጆችና ተማሪዎች ትኩረት ሰጥተውት ሊሠሩበት ይገባል፡፡

ሌላው ሁለቱንም ከፋፍሎ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ለግቢ ጉባኤያት ተማሪዎችም ሆኑ ለሌሎች የተሰጠው ጊዜ በጣም በቂ ነው፡፡ ብዙዎቹ የሚጨነቁት ጊዜ ያንሰኛል በማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ጊዜ የሚያንሰን ቢሆን ይጨምርልን ነበር፤ ስለዚህ ጊዜ ስለማያንሰን ያለንን ማብቃቃትና መከፋፈል የግድ ነው፡፡ ይህ በአንድ ጊዜ የሚመጣ ሳይሆን ቀስ በቀስ በመለማመድ የሚስተካከል ነው፡፡ ይህንንም ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን መማር፡፡ ለእያንዳንዱ አገልግሎቷ ዓመቱን ሙሉ በወቅት፣ በወራት፣ በቀናት፣ … በጊዜ ቅደም ተከተል ከፋፍላ ስትፈጽም ትገኛለችና፡፡

እግዚአብሔር አምላካችን መጀመሪያ ዓለምን ሲፈጥር በዕለተ እሑድ፣ ሰኑይ፣ ሠሉስ፣ … እያለ በየቀኑ የተለያዩ ፍጥረታትን ፈጥሯል፡፡ በስድስቱ ቀናት የፈጠራቸውን ፍጥረታት በአንድ ቀን መፍጠር ተስኖት አይደለም፡፡ እርሱ የሰጠንን ሕይወት በአግባቡ መምራት እንዳለብን ሲያስረዳን ነው፡፡ ሰዎች ነንና ዕረፍት እንደሚያስፈልገን ሲያስረዳን ደግሞ በስድስት ቀን

ፍጥረታትን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አረፈ፡፡ እግዚአብሔር ድካም ኖሮበት አይደለም ያረፈው፣ አርአያ ሊሆነን እንጂ፡፡

ለመንፈሳዊም ሆነ ለሥጋዊ ሕይወታችን ጊዜ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ በዚህ ጉዞ ውስጥ ለሚያጋጥሙ መሰናክሎች ሁሉ ዋጋ መክፈልን ይጠይቃል፡፡ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎችም በአፍላ የወጣትነት ዘመን ላይ ስለሚገኙ የዕድሜያቸው ጉዳይ ወሳኝነት አለው፡፡ በአሥራ ስምንት፣ በአሥራ ዘጠኝ ዓመታቸው ከወላጆቻቸው እጅ ተነጥለው ይወጣሉና ራሳቸውን ተቆጣጥረው ለመምራት ዋጋ ሊከፍሉ ይገባል፡፡ በሚሄዱበት ቦታ የማያውቁት ማኅበረሰብ፣ ባህል፣ አየር ንብረት፣ ... ይገጥማቸዋል፡፡ ጋምቤላ ተወልዶ ያደገው ደብረ ብርሃን ቢደርሰው ወይም በተቃራኒው ቢሆን ለመልመድ መጣር፣ ጊዜውንም እንደ አየር ጠባዩ ባህርይ ማመቻቸት ይገባል፡፡

ሌላው ከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ ለሚያወጣው ሕግና ደንብ ክርስትናቸውን በማይጎዳና በማያጋጫቸው ሁኔታ አስማምቶ መጓዝ ያስፈልጋል፡፡ ብዙዎች ፍርሃት ስለሚያድርባቸው ወደ ግቢ ጉባኤ ሄደው ከመማር ይልቅ መደበኛ ትምህርታቸው ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግን ይመርጣሉ፡፡ ከመንፈሳዊው ሕይወት ይልቅ ዓለማዊውን መንገድ ይከተላሉ፡፡ ራሳቸውን በፈለጉት መንገድ ለመምራት ምቹም ስለሚሆንላቸው ነፃነት ያገኙ እየመሰላቸው ለኃጢአት ይጋለጣሉ፡፡ በራሱ ክርስትናውም መጾም፣ መጸለይ፣ ቃለ እግዚአብሔር መማር፣ ማገልገልን ስለሚጠይቅ በትምህርቴ እሰንፋለሁ በማለት ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን በምትመራበት መንገድ ለመጓዝ ዳገት ስለሚሆንባቸው ይሸሻሉ፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሹመት ሊቀበል ሄዶ ስመ እግዚአብሔር እየተሰደበ ይሰማል፡፡ የሚያልፈውን ሥልጣን ሊቀበል ሄዶ የማያልፈው ሥልጣን (የእግዚአብሔር መንግሥት) ሊቀርበት መሆኑን ተረዳ፡፡ የሚያልፈው ሥልጣን ምን ያደርግልኛል? ብሎ ይዘውት ለመጡት አጃቢዎቹ በፈለጋችሁት ሂዱ በማለት ነፃ አውጥቶ ካሰናበታቸው በኋላ እርሱ ወደ ተጋድሎ ገባ፡፡ "እነሆ የታገሱትን ብፁዓን እንላቸዋለን" ተብለናልና ቅዱሳኑን አብነት በማድረግ መጋደል እንዳለብን ከቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ከቅድስት አፎሚያ፣ እና ከመሳሰሉት ሕይወት መማርን ይጠይቃል፡፡

የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጀምሮ በመምህሮቻቸውም ጭምር ኦርቶዶክሳዊ በመሆናቸው ብቻ ጫና ወይም ፈተና ሊገጥማቸው

ይችላል፡፡ ሶስና በአይሁድ መምህራን የገጠማት አስገዳጅ የዝሙት ጥያቄን እንዴት እንደተወጣችው መረዳት ይገባል፡፡ አንዲት እኅት አስተማሪዋ ውጤትን ምክንያት አድርጎ አታሎ ከመንፈሳዊ ሕይወቷ ሊያጎድላት፣ ከእግዚአብሔርም የሚለያትን የዝሙት ጥያቄ ቢያቀርብላትና ካልሆነ ውጤቷን እንደሚያበላሽ ቢያስፈራራት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ በትምህርቷ የሚደርስባትን ውጤት የማጣት ቀውስ እግዚአብሔርን በማመንና በእርሱ በመመካት እንደምትወጣው ማስብ ያስፈልጋል፡፡ ሶስናን አርአያ ማድረግ ይጠበቅባታል፡፡

መንፈሳዊውንም ሆነ ዓለማዊውን ዕውቀት ማዳበር፣ መትጋት ከተማሪዎች ይጠበቃል፡፡ መንፈሳዊው ሕይወታቸው ዓለማዊውን ትምህርት እንዳይማሩ ሊያግዳቸው አይገባም፡፡ መንፈሳዊ ሰው መሆን በዓለማዊው ትምህርት የበለጠ ውጤታማ መሆንን፣ ዘመኑን እንዲዋጁ መንገዱን ያመቻቻልና አንዱ አንዱን አያጠፋውም፡፡ በትምህርት ላይ ሳለን ሥራችን ትምህርታችን ነው፡፡ በትምህርታችን ውጤታማ ለመሆን ደግሞ እግዚአብሔር እንዲያግዘን ምሥጢሩንና ጥበቡን እንዲገልጽልን፣ ለተጠራንለትም ዓላማ ታምነን እንድንገኝ እርሱን መደገፍ ተገቢ ነው፡፡ መማራችን ብቻውን ለውጤት አያበቃንም፤ እግዚአብሔር ካላከናወነልን በከንቱ እንደክማለን፡፡ የሁሉም ነገር ጀማሪና ፈጻሚ እግዚአብሔር ነውና በእርሱ መመካት ያስፈልጋል፡፡ "የሚመካ ግን በእግዚአብሔር ይመካ" እንዲል፡፡ (፪ቆሮ.፲፥፲፯)

በመንፈሳዊውም ሆነ ዓለማዊ ሕይወታችን ውስጥ ዘወትር ሳንታክት መሥራት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁ ዝም ብሎ እኔ መንፈሳዊ ነኝ፣ ወይም እኔ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነኝ ማለት ትርፉ ውድቀት ነው፡፡ በጥር ድርሳነ ሚካኤል አንድ በጣም በሃይማኖቱ ጽኑ የነበረ ሰው ነበረ፡፡ ዕለት ዕለት ቅዱስ ሚካኤልን ጌታዬ ሆይ የዕለት ጉርሴን፣ የዓመት ልብሴን እያለ ይለምናል፤ ግን አይሠራም ሰነፍ ነው፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ተገለጠለትና "ወዳጄ ምን ሆነህ ነው አታርስ፣ አትቆፍር፣ አትነግድ፤ አዳም የተባለውን አልሰማህምን? "ወጥተህ ወርደህ በፊትህ ወዝ ብላ" ተብሏል እኮ፡፡ ሁል ጊዜ ባርክልኝ ትላለህ የምባርክልህ ነገር ምን አለህ?" ይለዋል፡፡ ሰውየው ግን መልስ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ እኛም የምንችለውን ማድረግ፣ መጣር ይጠበቅብናል ማለት ነው፡፡ ነቢዩ ነህምያ "የሰማይ አምላክ ያከናውልናል፤ እኛ ባርያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን" እንዳለው እኛ ጠበቅብንን ማድረግ፣ አምላካችን እግዚአብሔርም የልቡናችንን መሻት ማመን ይገባል፡፡ (ነህ.፪፥፳)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተቀበረ አራት ቀን ለሆነው አልዓዛር ድንጋዩን አንሡለት ብሏል፡፡ በታተመ መቃብር የተነሣ አምላክ አልዓዛርን ማስነሣት አቅቶት አይደለም፤ የኛ ድርሻ እንዳለበት ሲያመለክተን ነው እንጂ፡፡ የሞተውን ማስነሣት ደግሞ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው በመንፈሳዊም ሆነ በዓለማዊ ሕይወታቸው ሊተጉ፣ ራሳቸውንም በዕቅድና በጊዜ ቅደም ተከተል ለመምራት ቁርጠኛ ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሚፈታተናቸውንና እንዳሰቡት እንዳይጓዙ የሚያሰናክላቸውንም እንቅፋት ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መንገድ ቢጓዙ በሁለቱም በኩል የተሳለ ሰይፍ ይሆናሉ፡፡ መጀመሪያ የሁለቱንም አስፈላጊነት መረዳት፤ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሀገርን፣ ቤተሰቦቻቸውን ሊያኮሩ እንደሚገባቸው መረዳት፤ ከዚያም ጊዜ ሰጥቶ ለሁለቱም የሚገባውን መሥራት፤ ይህንንም ለማድረግ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆን ይገባል፡፡

ጉባኤ ቃና፡- ከእርስዎ ተሞክሮ አንጻር እንዴት ያዩታል?

ቀሲስ ዐቢይ፡- እኔ በግቢ ጉባኤ ውስጥ ሳለሁ የነበረው መልካም አጋጣሚም ሆነ ተግዳሮት ዛሬ ላይ ላይኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በአገልግሎት ላይ ያለኝ አመለካከትና ተሳትፎ ጠንካራ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ ወደ አገልግሎት ከመሮጤ የተነሣ አሁን ላይ ሆኜ ሳስተውለው አገልግሎቱ ቢያስደስተኝም ከዚያ በላይ የአብነት ትምህርቱን ለመማር ጥረት አለማድረጌ የምፀፀትበት ጊዜ አለ፡፡ ከአገልግሎት የተማርኩት እንዳለ ሆኖ ከመምህራን እግር ሥር ቁጭ ብዬ መማር የነበረብኝ ብዙ ትምህርቶች ነበሩ፡፡ በእርግጥ ካለፈ በኋላ ነው የገባኝ፡፡ በውጤት በኩል አብረን ከተመረቅነው ፲፭ ተማሪዎች የመጀመሪያ ወይም ሰቃይ የሚባለው ደረጃ ላይ ነበርኩ፡፡ ለምሳሌ ሐዲስ ኪዳንን ተምሬ መውጣት እችል ነበር፡፡ ከእኔ በላይ የነበሩና ሜዳልያ ተሸልመው የወጡት በግቢ ጉባኤ አገልግሎት ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸው ናቸው፡፡ በግቢ ጉባኤ ውስጥ መሳተፍ፣ መንፈሳዊ ሕይወትን ማጠንከር የበለጠ ኃላፊነት እንዲሰማን፣ ቤተ ክርስቲያንና ሀገርን ማገልገል እንደሚገባን መሠረት የምንጥልበት ነው፡፡

ጉባኤ ቃና፡- ዓለማዊውን እና መንፈሳዊውን ትምህርት ሁለቱንም መያዝ የሚያስከትለው ጉዳት አለ? ቢያብራሩልን?

ቀሲስ ዐቢይ፡- እንግዲህ አንድ ነገር ሙሉ ለሙሉ ጉዳት አለው ወይም

የለውም ማለት አይቻልም። ለመብላት መሥራት አለብን፣ ስንሠራ ደግሞ መውጣት መውረድ፣ ላብ ማውጣት፣ መድከምን ይጠይቃል። ራስን በመንፈሳዊም በዓለማዊም ዕውቀት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ደግሞ ራስን በዕቅድ መምራት አስፈላጊ ነው። ወደ አሰቡት ለመድረስ በርካታ ውጣ ውረዶች ይኖራሉ። የጓደኛ ተጽእኖ፣ የሥጋዊ ፍላጎት ማየል፣ ጊዜን በአግባቡ ያለመጠቀም፣ ...የመሳሰሉት ወደታሰበው ውጤት ላለመድረስ እንቅፋቶች ይሆናሉ። ነገር ግን በድል መወጣትን ይጠይቃልና በጽናት ችግሮቹን በመቋቋም የሚገኘው ክብር ታላቅ ነውና በትዕግሥት ማለፍ ይገባል። ስለዚህ ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ ከፍተኛ ስለሆነ፣ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔርም የሚያደርስ መሆኑን መረዳት ይገባል።

ጉባኤ ቃና፡- ሁለቱንም አጣምሮ በመማር ሊገኝ የሚችለው ጥቅም ምንድነው?

ቀሲስ ዓቢይ፡- ጥቅሞቹን አንድ፣ ሁለት እያልን መመለከት እንችላለን። የመጀመሪያው መንፈሳዊ ሕይወታችን ይበረታል፣ የመንግሥቱ ወራሾችም እንሆናለን። መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን "ሰዎች እንዳይስቱ እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረም፤ ኃጢአተኞች በልባቸው አስበው በቃላቸው ተናግረው ጠሩት፤ ወዳጅም አደረጉት" ይላል (ጥበ.፩፥፲፪)። ስለዚህ እግዚአብሔር ሞትን ካልፈጠረ እኛን ሕያው አድርጎ በመንግሥተ ሰማያት ሊያኖረንና እንደ መላእክት እርሱን እያመሰገንን፣ ስሙን ቀድሰን፣ ክብሩን እንድንወርስ ለማድረግ ነው። በዓለማዊ ሕይወታችንም እግዚአብሔርን በመፍራትና እንደ ቃሉም በመጓዝ መልካም ሥራንም እየሠራን የተሳካልን እንሆናለን። ብንበድል እንኳን ዕለት ዕለት ንስሓ እየገባን፣ በሃይማኖታችን ጸንተን ንጽሕናችንን ጠብቀን እንኖራለን፤ የሕሊና ዕረፍትም እናገኛለን።

ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል እና ጓደኞቹ በስደት፣ በማያውቁት ሀገርና ሕዝብ ፊት ሞገስን ያገኙት ከእግዚአብሔር አምልኮ ባለመለየታቸው ነው። ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው አልፈው በዓለማዊው ሕይወታቸው እግዚአብሔርንና ሰውን ማስደሰት በመቻላቸው ነው። ስለዚህ በየግቢ ጉባኤያቱ ሜዳሊያ እየያዙ የሚወጡ እኅት ወንድሞቻችን ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው እና ለመደበኛ ትምህርታቸው ጊዜ ሰጥተው ለተጠሩለት ዓላማ ታምነው ተገኝተዋልና በውጤት ታጅበው ይወጣሉ። የቀደሙት ወንድሞችና እኅቶችንም አርአያ

መከተል ይገባል፡፡ በትምህርት ሰዓት በቂ ጊዜ ወስዶ መማር፣ ማጥናት፣ ለመንፈሳዊ አገልግሎት፣ ለትምህርት የምናውለውን ጊዜንም በአግባቡ መጠቀም መቻል ከግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ይጠበቃል፡፡ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ ማስፈራሪያዎችን ማለትም ጊዜ አይበቃህም፣ በትምህርትህ ትደክማለህ እያሉ የሚያስፈራሩትን ታግሶ ሠርቶ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ራስን የመምራት ክህሎት እናዳብራለን፣ መንፈሳዊ ሕይወታችንንም እናጠነክራለን፣ በትምህርታችንም ውጤታማ እንሆናለን፡፡

ጉባኤ ቃና፡- በመጨረሻም ማጠቃለያ ሰጥተው ብናጠቃልል?

ቀሲስ ዐቢይ፡- እንግዲህ "ለጥበበኛ ሰው አንዲት ቃል ትበቃለች" ይላል ጠቢቡ ሰሎሞን ብዙ ነጥቦችን አንስተናል፡፡ ሰው ሲፈጠር በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል ነው የተፈጠረው እና በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል የተፈጠረ ሰው ደግሞ በእግዚአብሔር ሕግ፣ ፈቃድና ትእዛዝ ሊኖር ነው የሚገባው፡፡ ነገር ግን ዓለም ለዚህ ምቹ ሆና አልተገኘችምና ይህንን በጽናት አልፎ መንፈሳዊ ሕይወትን በመላበስ የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ ለመኖር መትጋት ከኦርቶዶክሳውያን ይጠበቃል፡፡ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ይህንን ሸክም ተሸክሟል ማለት ይቻላል፡፡ አባቶቻችን የድርሻቸውን ተወጥተው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን፣ ነቅዕ፣ ጥርጥር የሌለባትን ሃይማኖት አስረክበውን አልፈዋልና እነርሱን አርአያ በማድረግ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ የመጣውን ስደትና መከራ እግዚአብሔር ወደ ምሕረት ይለውጥልን ዘንድ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ በተለይም የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ዓለማዊውንና መንፈሳዊውን ዓለም የመረዳት አቅማቸው ከፍተኛ በመሆኑ ራሳቸውን በማብቃት ዘወትር በአገልግሎት መጽናት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚህ ዘመን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በመከራ ውስጥ ትገኛለች፡፡ ይህንን መከራ የሚያስወግድ ከባሕሩ ማዕበልና ሞገድ ከስጥመት የሚታደጋት ትውልድ ትፈልጋለች፡፡ ስለዚህ ከግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ብዙ ይጠበቃል፡፡ እግዚአብሔርን ማመን፣ በቅዱሳን ተራዳኢነትና ቃል ኪዳን መታመን ከቻልን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ሀገራችንን መታደግ እንችላለን፡፡ "እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ የኃጢአትንም ጭንቀት ከእኛ አስወግደን

በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ" ይላል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ። (ዕብ.፲፪፥፩) ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የመላእክትም ጥበቃ አይለያትም። ይህ የሚሆነው ግን በተሠማራንበት ሁሉ የሚጠበቅብንን ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም አገልግሎት ስናበረክት ነው። ልባችንን ለእግዚአብሔር ሰጥተን ስንጸልይ፣ ንስሓ ስንገባ ነውና ዘወትር ወደ እግዚአብሔር መጮኽ፣ አገልግሎታችንም ማጠናከር ይገባል።

ጉባኤ ቃና፡- እግዚአብሔር ይስጥልን።

ቀሲስ ዐቢይ፡- እኔም እግዚአብሔር ስጥልን፣ አመሰግናለሁ።

ብሂለ አበው

ያለ ጸሎት መንፈሳዊ ነኝ የሚል ሰው እሳት መካከል ገብቶ የሚጫወትን የእሳት ራትን ይመስላል። (ማር ይስሐቅ)

ልጄ ሆይ አንተ በራስህ ላይ ስትፍረድ እግዚአብሔር ፍርዱን ያነሳልሃል፤ አንተ በራስህ ላይ ባትፈርድ ግን እግዚአብሔር ይፈርድብሀል።

(ታላቁ መቃሪዮስ)

ክርስትና የሚጀምረው ከተግባር እንጂ ከወሬ አይደለም። ሕይወታችን በጥቅስ ተገንዞ በጥቅስ የተቀበረ ከሕይወትና ከሥራ የተለየ እንዲሆን አንፍቀድለት። /ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ/

ዘመን ማለት አንተ ነህ ። አንተ ሰላማዊ ስትሆን ሰላማዊ ትሆናለች። አንተ የከፋህ እንደሆነ ትከፋለች። / አንጋረ ፈላስፋ/

ራስህን ለማየት ወደ መስታወት ብትመለከት ውበትህን ወይም ጉድለትህን ያሳይሀል። ምንም ነገር እንዳታይ ታደርግ ዘንድ ከመስታወቱ መሰወር አትችልም። ማንም ሊያመልጥበት በማይችለው በፍርድ ቀንም እንዲሁ ይሆናል። /አንጋረ ፈላስፋ/

ባልንጀራ

በእንዳለ ደምስስ

ባልንጀራ የሚለውን ቃል ደስታ ተክለ ወልድ በመዝገበ ቃላት መጽሐፋቸው፦ "እኩያ፣ ባልደረባ፣ አቻ፣ አብሮ አደግ ጓደኛ፣ እንጀራ አቋራሽ" በ ማለት ሲተረጉሙት ባልንጀርነትን ደግሞ "እኩያነት፣ ባልደረብነት" በማለት ይፈቱታል።

ባልንጀራ ክፉም ሆነ መልካም ነገር ሲገጥመን አብሮ የሚያዝንና የሚደሰት የልብ ወዳጅ፣ መልካሙን መንገድ የሚያሳይ፣ … ማለታችን ነው። ባልንጀርነት አብሮ በማደግ፣ አብሮ በመማር፣ አብሮ በመሥራት እንዲሁም በሙያ አጋርነት በመሳሰሉት ሁኔታዎች ሊፈጠር ይችላል። ይህ የባልንጀርነት ቁርኝት እየዳበረ የሚመጣ እንደመሆኑ መጠን በተለያዩ ምክንያቶችም ሊፈርስ ወይም ሊከስም ይችላል።

ክፉ ባልንጀራ የሌላውን ሕይወት ያጨልማል፣ መልካምን ከማሰብና ከማድረግ ይልቅ ክፉ ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ተግባራዊም ያደርጋል። አባቶቻችን ለዚህ ነው "ክፉ ባልንጀራ አይግጠምህ፤ ከክፉ ባልንጀራ ራቅ" እያሉ የሚመክሩት። ክፉ ባልንጀራ መልካም የሆነውን ወዳጁን ጠባይ ቀስ በቀስ በመለወጥ በሄደበት እንዲሄድ፣ በዋለበት እንዲውል፣ ከመልካም ቦታዎች ይልቅ ኃጢአትን ወደሚሠራባቸው ስፍራዎች ማለትም መንፈሳዊ ቦታዎችን አስጥሎ ወደ ጭፈራ ቤቶች፣ ዝሙት ወደሚሠራባቸውና ልዩ ልዩ ያልተገቡና በማኅበረሰቡም በእግዚአብሔርም የተጠሉ ተግባራት ወደሚከናወንባቸው ቦታዎች በመሄድ ጠፍተው እንዲቀሩ ምክንያት ይሆናል።

ለዚህ እንደ ምሳሌ የሔዋንና የዲያብሎስ ወዳጅነት ማየት ይቻላል። ሰይጣን ከነበረው ክብር አምላክነትን በመሻቱ ምክንያት ከተጣለ በኋላ ለክፉ ሥራው ተባባሪ ለማግኘት በእባብ ላይ አድሮ ወደ ሔዋን ቀረበ። የአዳምና ሔዋን

በገነት ውስጥ በተድላ በደስታ መኖር አበሳጭቶታል፡፡ እኔ ወድቄ ሌላው ለምን ይኖራል? በሚል በእባብ ላይ አድሮ ከሔዋን ጋር ባልንጀርነትን መሠረተ፡፡ እባብም ሴቲቱን "እግዚአብሔር በገነት ካለው ዛፍ ሁሉ አትብሉ ያላችሁ ለምንድነው?" አላት፡፡ ሴቲቱም "በገነት መካከል ካለው ከሚያፈራው ዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፤ እግዚአብሔር አለ "እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ፣ አትንኩትም" አለን በማለት አስረዳችው፡፡ (ዘፍ. ፫፥፫)

በእባብ ላይ ያደረው ሰይጣንም "ሞትን አትሞቱም፤ ከእርሱ በበላችሁ ቀን ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ፡፡" አላት፡፡ ሔዋንም እጅግ ለመብላት ጓጓች፤ ከዕፀ በለሱ ቀጥፋም ለአዳም ሰጠችው፤ ሁለቱም በመብላታቸው ዐይኖቻቸው ተከፈቱ፤ እግዚአብሔርንም አስቆጡት፤ ከገነት ወደ ምድረ ፋይድ ተጣሉ፡፡ ይህ ሁሉ ከክፉ ባልንጀራ ጋር ወዳጅነት መመሠረት ያስከተለው ጥፋት ነው፡፡

ባልንጀርነትን ከሚያበላሹ ነገሮች መካከል ጥቂቶቹን ብንመለከት፡-

በመንፈሳዊ ሕይወት መዛል፡- በመንፈሳዊ ሕይወት ስንዝል ለሥጋዊ ፍላጎት ተላልፈን እንሰጣለን፡፡ ነፍሳችን በሥጋችን ላይ ትሠለጥናለች፡፡ በተለይ በወጣትነት ዘመናችን ስሜታዊነት ስለሚያይልብን ይህንንም ያንንም ለመሞከር በምናደረግው ጥረት ውስጥ መንፈሳዊ ሕይወታችን ይጎዳል፡፡ በዚህ ወቅት መንፈሳውያን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችንን ትተን ከማይመስሉን ጋር የሥጋን ሥራ ለመሥራት እንፈጥናል፡፡ ይህ ደግሞ በሕወታችን ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር እንኖራለን፣ እናሳካዋለንም ብለን ያሰብናቸው ነገሮች ሁሉ ከንቱ ሆነው ይቀራሉ፡፡ ቀድሞ የነበረንን ማንነት እያጣን መንፈሳዊነትን እርግፍ አድርገን እንድንተው ያደርገናል፡፡

ነገር ግን ከዚህ ይልቅ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ሊያጠናክሩልን፣ ብንወድቅ የሚያነሡንን፣ ብንደክም የሚያበረቱንን መልካም ወንድሞችና እኅቶችን መጠጋት ይገባል፡፡

የአቻ ግፊት፡- በብዙ ወጣቶች ዘንድ በተለይም በግቢ ጉባኤት ተማሪዎች ዘንድ ጎልተው ከሚታዩ ችግሮች አንዱ የአቻ ግፊት ነው፡፡ ከመንፈሳዊው

ሕይወት እንድንወጣ ብልጭልጩን ዓለም እያሳዩ ከእግዚአብሔር እንድንለይ ከሚያደርጉን አቻዎቻችን መራቅ ተገቢ ነው፡፡ በአቻ ግፊት ምክንያት አዲስ ጠባይ እንድንይዝና ለማይገቡ ክፉ ጠባይት ተላልፈን እንዳንሰጥ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ "ሁሉን መርምሩ፤ መልካም የሆነው ያዙ" ተብለናልና፡፡ (፩ተሰ. ፭፥፳፩)

በወጣትነት ዘመናችን በተለይም በግቢ ጉባኤ ሕይወታችን ውስጥ መልካም እየመሰሉን ከእግዚአብሔር አንድነት ከሚለዩን በዙሪያችን ካሉ ባልንጀሮቻችን መራቅ ይጠበቅብናል፡፡ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እንቅፋት የሆኑትን በመራቅ መንፈሳዊ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችንን መከተል፣ መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብና ከመንፈሳዊ ሕይወታችን ሊያርቁን ከሚችሉ አካባቢዎች መራቅና ጊዜያችንን በአግባቡ በመምራት በአቻ ግፊት እንዳንወድቅ ይረዳናል፡፡

የሚጠቅመንና የሚጎዳንን መለየት፣ አባቶችን ማማከር፣ ወደ መልካም መንገድ ሊመሩን የሚችሉ አርአያ የምናደርጋቸውን ወንድሞችና እኅቶችን መከተል፣ ዘወትር በመንፈሳዊ ሕይወታችን በመትጋት የአቻ ግፊትን ተጽእኖ በመቋቋም በራስ መተማመንን ማጎልበት ይጠበቅብናል፡፡

ከላይ ከተመለከትናቸው ውጪ ክፉ ባልንጀርነት የሚፈጥረብን ተጽእኖ ቀላል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ክፉ ባልንጀርነት አለመተማመንን፣ ክፉ ጠባያት እንድንለምድ፣ ራስን ብቻ እንደንወድ፣ … ከመንፈሳዊነት እንድንወጣ ሊያደርገን ይችላል፡፡

ሀ. አለመተማመን፡- በባልንጀሮች መካከል መልካሙን ግንኙነት ከማጠናከር ፋንታ የግል ጥቅምን በመሻት ወይም በባልንጀራ ላይ በመቅናትና የባልንጀራን የሆነን ሁሉ በመመኘት በሚፈጠሩ ያልተገቡ ጠባያትና ድርጊቶች ምክንያት ጤናማ የባልንጀርነት ግንኙነት ሊበላሽ ይችላል፡፡ ይህም በባልንጀሮች መካከል አለመተማመንን ይፈጥራል፡፡

ራስን ልዩ አድርጎ መቁጠር፣ በባልንጀራ ላይ የበላይ ሆኖ ለመታየት መጣር፣ ራስን ብቻ መውደድ፣ … ወዘተ በሁለቱ አካላት መካከል አለመተማንን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፡፡ ይህም እስከ ጠላትነት ሊያደረስ የሚችል አካሄድ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በሥነ ምግባር ያለመታነጽ፣ ከመንፈሳዊ ሕይወት

ማፈንገጥና ለሥጋ ምኞትና ፍላጎት ብቻ ማደር በጎውን መንገድ እንዳናስብ መንገዱን ስለሚዘጋ ባልንጀራን ወደ ሥጋዊ አስተሳሳብና ድርጊት እንዲመራ በር ይከፍታል፡፡

ለ. ክፉ ጠባያትን ማስለመድ፡- በባልንጀሮች መካከል መልካም ጠባያት እንዳለ ሁሉ ክፉ የምንላቸው ጠባያትን ሊንጸባረቁ ይችላሉ፡፡ በተለይም የጓደኛ አመራረጣችንና አያያዛችን ወደማንፈልገው አካሄድ ሊመራን ይችላል፡፡ ይህም ሕይወታችንን በመልካም ሥነ ምግባር እንዳንመራ እንቅፋት ይሆንብናል፡፡ ለመሆኑ ባልንጀራችን ማነው? በሕይወት፣ በባህል፣ በእምነት እንመስለዋለን? ውሎውን እንውላለን? በሃይማኖት አንድ ነን? የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ትውፊትና ሥርዓትን ይጠብቃል? እነዚህንና ሌሎችንም መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ቤተ ክርስቲያንን አስጥሎ ለሥጋ ብቻ በማድላት ከጸሎት ይልቅ ሙዚቃን፣ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ይልቅ ሥጋን ለመስደሰት የሚፈጥን ከሆነ ይህ ክፉ የክፉ ባልንጀራ ጠባይ ነውና መራቅ ያስፈልጋል፡፡ ሁል ጊዜ ከመልካም ይልቅ እግዚአብሔርንና አገልግሎትን የሚያስጥሉ ክፉ ጠባያትን የሚያስለምደን በመሆኑ ከዚህ ጋር ከመተባበር ልንቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ ከማይመስሉን ጋር በክፉ መጠመድ አይገባም፡፡ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋልና፡፡ (፩ቆሮ. ፲፭፥፴፫)

ሐ. ራስን ብቻ መውደድ፡- ራሳችንን ብቻ የምንወድ ከሆነ ለሌላው ግድ አይኖረንም፡፡ ሁል ጊዜ ራሳችንን በማስቀደማችን ለሌሎች እንዳንኖር፣ ለባንጀሮቻችን ትኩረት እንዳንሰጥና ባልንጀሮቻችን እኛ በቀደድነው መንገድ ብቻ እንዲጓዙ ተጽእኖ እናሳድራለን፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ “እኔ ብቻ” አስተሳሰብን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጎለብት ስለሚያደርግ ከምናመልከው እግዚአብሔር ይለየናል፤ ወደ ክፋትም ይመራናል፡፡ ራሳችንን ብቻ በወደድን ቁጥር ለሌላው ክብር ለመስጠት እንቸገራለን፡፡ ስለዚህ ባልንጀራችን በተቸገረ ጊዜ ከአጠገቡ ከመቆም ይልቅ ውድቀቱ እንዲፋጠን ግፊት እናደርጋለን፡፡ በትምህርትም ይሁን በልዩ ልዩ ዕውቀት፣ በሀብት፣ ... የሚበልጠን መስሎ ከተሰማን ከእርሱ ከመማር ይልቅ ለመጣል ጥረት እናደርጋለን፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ሳንሆን እንድንቀር ያደርግናል፡፡

በግቢ ጉባኤያት ውስጥ የምንሳተፈው እርስ በእርስ ተደረዳድተን ስንሳተፍ አንዱ ያላወቀውን በማሳወቅ፣ በመረዳዳት መጓዝ እንጂ ሊበልጠኝ ይችላል በሚል ሰበብ በባልንጀራ ላይ ክፉ ማድረግን ልንጸየፍ ይገባል። ግቢ ጉባኤያት እግዚአብሔርን የምናውቅበት፣ በዕውቀት በጥበብ የምንበለጽግበትና መልካም ባልንጀርነትን የምንመሠረትበት ለሌሎችም አርአያ ሆነን የምንገኝበት መልካም አጋጣሚ መሆኑን በመረዳት ራስን ብቻ ከመውደድ አልፈን መንፈሳዊ ፍሬ ልናፈራ ይጠበቅብናል።

ባልንጀራን መውደድ በረከትን ያሰጣል፤ ከእግዚአብሔርም ጋር ሕብረት እንድንፈጠር ይረዳናል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ሲሆን የእኛን ሥጋ ለብሷልና እኛን ያድነን ዘንድ በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ላይ ተሰቅሏል። ሰውን በመውደዱ እስከ ሞት ድረስም የታመነ ሆነ። "ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ያለ እንደሆነ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለም" እንዲል (ዮሐ. ፲፭፥፲፫) ቅዱስ ዮሐንስ።

ክፉ ባልንጀርነት በተመለከተ እነዚህን ከላይ የጠቀስናቸውን ነጥቦች አነሣን እንጂ ሌሎችንም ማንሣት ይቻላል።

በተቃራኒው ራስን ከክፉ ባልንጀራ በማራቅ መልካም ባልንጀርነትን መመሥረትና በምግባር በሃይማኖት ታንጾ መኖር ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት እንድናጠናክር ያደርገናል።

መልካም ባልንጀርነት

ሰዎች በሚኖራቸው የእርስ በእርስ የሕይወት መስተጋብር መልካም ባልንጀርነትን ሊመሠርቱ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል የነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት እና የነቢዩ ናታን ግንኙነትን ማንሣት እንችላለን።

ነቢዩ ዳዊት የወዳጁንና የጦር አበጋዙ ኦርዮን ሚስት "የባልንጀራህን ሚስት፣ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ" (ዘጸ. ፳፥፲፯) የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ ቤርሳቤህን በማስነወሩና እርሷም በማርገዟ ኦርዮንን ማስገደል አማራጭ አድርጎ ወሰደው። ጦር ሜዳ ሳለም አስገደለው። እግዚአብሔርም በዝምታ አላለፈውም። ይገስጸው ዘንድ ባልንጀራውን ነቢዩ ናታንን ላከበት።

ነቢዩ ናታንም እኔ ስለ ባልንጀራዬ ምን አገባኝ ሳይል ብልሃት በተሞላበት

መንገድ በምሳሌ አስረድቶ ስለ ጥፋቱ ነግሮ በንስሓ እንዲመለስ የድርሻውን ተወጣ፡፡ ይህ የመልካም ባልንጀርነት ውጤት ነው፡፡ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ይላል፡፡ "ልቡ ንጹህ የሆነ፣ እጆቹም የነጹ፣ በነፍሱ ላይ ከንቱ ያልወሰደ፤ ለባልንጀራውም በሽንገላ ያልማለ፣ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን ይቀበላል" ይላል፡፡ (መዝ. ፳፫፥፬)

መልካም ባልንጀርነትን ሊያጠነክሩ የሚችሉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል ጥቂቶቹን እንመለከት፡-

ሀ. ማመንና መታመን፡- በቅርባችን ያሉትን እናትና አባታችን፣ ቤተሰቦቻንን፣ ጓደኞቻችንን፣ ወይም በጎ ነገር ያደረጉልንን ልናምን እንችላለን፡፡ ነገር ግን ከሁሉም በፊት እግዚአብሔርን ማመን ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክቱ "በእርሱም እጸና ዘንድ ዛሬ የኦሪት ጽድቅ ሳይኖረኝ ክርስቶስን በማመን ከእግዚአብሔር የሚገኝ ጽድቅ አለኝ እንጂ፡፡" (ፊልጵ. ፫፥፱) በማለት እግዚአብሔርን ማመን ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ማመን ብቻ ሳይሆን መታመንም እንደሚያስፈልግ ሲያመለክት ደግሞ "የተጠራህለትንና በብዙ ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘለዓለምን ሕይወት ለመቀበል መልካሙን የሃይማኖት ገድል ተጋደል" (ጢሞ. ፮፥፲፪) ሲል ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስን እንዳሳሰበው ላመኑት ነገር ታምኖ መገኘትን አስፈላጊነት ያሳየናል፡፡ በዚህም መሠረት መልካም ባልንጀርነትን ለመመሥረት ጓደኛን ማመን፣ እንዲሁም ራስም ታምኖ መገኘት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎችን ችግር ማንሣት ያስፈልጋል፡፡

የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ከቤተሰብ መራቃቸው፣ ራሳቸውን እንዲመሩ ነጻነትም ስለሚሰማቸው ጓደኛ ለመያዝ የሚያደርጉት ጥረት ላይ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ሥጋዊውን በማሰብና በማድረግ ለተጠሩለት ዓላማ ታምነው መገኘት ይሳናቸዋል፡፡ ስለዚህ ጓደኛዬ ማነው? ሊሉ ይገባል፡፡ በሃይማኖት የሚመስላቸውን፣ ለአገልግሎት የሚያበረታቸው፣ ምሳሌም የሚሆናቸው፣ በትምህርታቸውም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሊደጋገፉ የሚችሉ መሰዮቻቸውን መምረጥ ይገባቸዋል፡፡ ብዙዎች ውጤት

አልባ ሆነው የሚቀሩት ለሥጋዊ ፍላጎታቸው በማድላት በሚፈጽሙት ያልተጋባ ድርጊት ከዓላማቸው ሲሰናከሉ እንመለከታለንና ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የሚያምኑትና እነርሱም ሊታመኑለት የሚችሉትን ባልንጀራ መያዝ ያስፈልጋል።

ለ. ራስን አሳልፎ መስጠት፡- መልካም ባልንጀርነት ራስን አሳልፎ እስከ መስጠት የሚደርስ ነው። ባልንጀራህ በሚደርስበት ችግር ተካፋይ በመሆን ቢወድቅ ማንሣትን፣ ቢቸገር የችግሩ ተካፋይ መሆንን፣ ሁል ጊዜም መልካምን መመኘት ይጠይቃል።

ባልንጀርነትን ለማጽናት ማመንና መታመን እንደሚገባ ሁሉ ባልንጀራ በተቸገረ ጊዜ ከጎኑ በመሆን ደስታውንም ሆነ ችግሩን መካፈል ይገባል። ይህንንም ችግር ለመፍታት በሚደረግ ጥረት ውስጥ ስለ ባልንጀራ/ጓደኛ ራስን አሳልፎ እስከ መስጠት የሚደርስ እንኳ ቢሆን መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት መክፈል የመልካም ባልንጀርነት መገለጫ ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ላይ አድሮ "ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ፤ ቸር ጠባቂ ስለ በጎቹ ነፍሱ አሳልፎ ይሰጣል" በማለት እንደተናገረው ጌታችን የአዳምና የልጆቹን በደል ተሸክሞ በመስቀል ላይ ራሱን አሳልፎ በመስጠት በመስቀል ላይ ውሏል። (ዮሐ. ፲፥፲፩) የሰውን ልጆች ነጻ ያወጣ ዘንድ ነፍሱን እስከመስጠት ታማኝ፤ ቤዛም ሆነ። ስለ ሌሎች ራስን አሳልፎ መስጠትን ከጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንማራለን። "እንደ ሰውም ሆኖ ራሱን አዋረደ፤ ለሞት እስከ መድረስም ታዘዘ" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ጽፏል። (ፊልጵ. ፪፥፰)። መልካም ባልንጀራም ስለ ወዳጁ እስከ ሞት ድረስ እንኳ ቢሆን የታመነ ሊሆን ይገባዋል። "ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" (ዮሐ. ፲፭፥፲፫) እንዲል።

መልካምን ማድረግ፡- የባልንጀርነት መገለጫ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ለባልንጀራ መልካምን ማድረግ ነው። "መልካም ሰው ከልቡ መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል"ና (ማቴ. ፲፪፥፴፭) በማለት እንደገለጸው ሁል ጊዜ ስለ ባልንጀራ መጸለይ፣ በችግሩም ጊዜ አብሮ መቆምን፣ በሰላሙም ጊዜ አለመለየት፣ ከባልንጀራም ጋር መሆን ይገባል። በዚህም የእግዚአብሔርን በረከት ይገኛል። "ሰላምን

እተውላችኋለሁ፤ ሰላሙንም እሰጣችኋላሁ፣ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚ ሰጠው አይደለም፤ ልባችሁ አይደንግጥ፣ አትፍሩም” ይለናል፡፡ (ዮሐ. ፲፬፥፳፯)

ትእዛዛትን መጠበቅ፡- ከስድስቱ ትእዛዛተ ወንጌል አንዱ “ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ” የሚል ነው፡፡ ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድ ስንል ከልብ በመነጨ ፍቅር ተመሥርተን ውጣ ውረዱን፣ ደስታም ሆነ ሐዘኑን መጋራትን ያመለክታል፡፡ ከመቀበል ይልቅ መስጠት ላይ ትኩረት ያደረጋል ባልንጀርነት፡፡

ትእዛዛትን መጠበቅ ከቻልን ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ያለን ግንኙነት የጠበቀ ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት ከክፉ እንርቃለን፡፡ “ደግ ሰው ከመልካም ልቡ መልካም ነገርን ያወጣል” እንዲል፡፡ (ማቴ. ፲፪፥፴፫) ባልንጀራን ወደ ትክክለኛው መንገድ መምራት የመልካም ባልንጀርነት መገለጫ ነው፡፡ ትእዛዛትን የሚጠብቅ ሰው በባልንጀራው ላይ ክፉ ነገርም አያደርግም፡፡

በአጠቃላይ በሃይማኖት፣ በምግባር ታንጾ የሚኖር ሰው ለባልንጀራው ፍቅር ይኖረዋል፡፡ በባልንጀራው ላይ ክፉም አያደርግም፤ ሁል ጊዜ በባልንጀራው ደስታ እርሱም ይደሰታል እንጂ፡፡ ሌላውን መውደድ ስንችል እንግዚአብሔርን እንወዳለን፤ እርሱም ይወደናል፡፡ “… ባልንጀራህንም እንደ ራስህ መውደድ ከመባና ከመሥዋዕት ሁሉ ይበልጣል” ነው የተባለነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈላቸው መልእክቱ “ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል” (፩ቆሮ. ፲፭፥፴፫) ብሎ እንደተናገረው ከክፉ ባልንጀራ ርቀን፣ ክፉ የሆነውንና ከባልንጀራችን የወረስነው ክፉ ዐመል አስወግደን መልካምን እያደረገን እንኖር ዘንድ ይገባል፡፡

የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለየን፡፡ አሜን፡፡

ሠ ሰናክል

በእንዳለ ደምስስ

የሠርጉ አዳራሽ ጥሪ በተደረገላቸው ታዳሚዎች ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቷል፡፡ ወጣቱም፣ ሽማግሌውም፣ ሴቱም ወንዱም የክት ልብሳቸውን ለብሰው በተያዘላቸው ስፍራ ተቀምጠዋል፡፡ ወደ አዳራሹ ለሚገቡ ታዳሚዎች ደግሞ አስተናጋጆች ቦታ ለመስጠት ይጣደፋሉ፡፡ የሴቶቹ አለባበስና ጸጉር አሠራር ለትእይንተ ፋሽን የሚወዳደሩ አስመስሏቸዋል፡፡ ለሙሽሮች ከተዘጋጀው መድረክ ጀምሮ እስከ በሩ ድረስ የተዘረጋው ቀይ ምንጣፍ ለመርገጥ ያሳሳል፣ አዳራሹ ልዩ ልዩ ሕብረ ቀለማት ባላቸው የመድረክ መብራቶች፣ በነጫጭ ፕላስቲክ አበባዎች አሽብርቋል፤ ወንበሮችን ከበው በተሰየሙት ጠረጴዛዎች ላይ በተለያዩ ቅርጾች የተዘጋጁ ነጭና ሮዝ አበባዎች በወርቃማ ማስቀመጫዎች ተደርገው መሐል ላይ ተሰይመዋል፡፡ አበባዎች በየጠረጴዛው የተደረደሩት የመጠጥ ዓይነቶች ለብዙዎቹ ታዳሚዎች በስም፣ ወይም በፊልሞች ላይ እንጂ አይተው የማያውቁ በሚመስል ስሜት አንዳንዶቹ በግርምት ጠርሙሶቹን እያገላበጡ ያያሉ፡፡ አዳራሹ ታዳሚዎች በተቀቧቸው ልዩ ልዩ ሽቶዎች ጠረን ታውዷል፡፡ የሙሽሮች ቤተሰቦች፣ አስተናባሪዎች ወዲህ ወዲያ እያሉ የጎደለውን ለመሙላት፣ እንግዶችንም ለመቀበል ይፋጠናሉ፡፡

ለምለም፣ ፌቨን እና ሳምራዊት ስድስት ኪሎ ከሚገኘው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ ሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ሲሆኑ በጓደኛቸው ሉሊት ወንድም ሠርግ ላይ ለመታደም ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን መገናኛ ከሚገኘው ከሠርግ አዳራሹ ደረሱ፡፡ ከለምለም በስተቀር ሁለቱም ጓደኞቿ ካሏቸው ልብሶች አንዱን ትተው ሌላውን ሲሞከሩ ቆይተው ለእይታ የሚያጋልጣቸውን አለባበስ መርጠው ለብሰዋል፡፡ ለምለም ምንም እንኳን የክፍል ጓደኛቸው ብትሆንም ከክፍለ ሀገር መምጣቷ፣ ከልጅነት ጀምሮ

በሰንበት ት/ቤት ውስጥ ማደጓና ለመንፈሳዊ ሕይወት ካላት ጥልቅ ፍቅር የተነሣ ረጋ፣ በአለባበሷም ሆነ በአነጋገሯ ቁጥብነት ይታይባታል። ሌሎቹ የክፍል ጓደኞቿ ከመንፈሳዊነት የራቁ በመሆናቸው ከክፍል ውጪ ቅርበቷ የተገደበ ነው። ከመንፈሳዊ ሥርግ ውጪ መገኘት ባትፈልግም ሉሊትን ስለምታከብራት፣ በችግሯ ጊዜም ደራሿ በመሆኗ ለመገኘት ወስናለች። የጓደኞቿ መቅበጥበጥ ደግሞ አላማራትም።

ሦስቱም አዳራሹ ከሚገኝበት ግቢ ደርሰው የጥሪ ወረቀታቸውን አሳይተው ገቡ። ግቢው በአረንጓዴ ሳር፣ አጸዶችና አበባዎች ተውቦ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ዘመናዊ አግዳሚ ወንበሮች ተቀምጠው ይታያሉ። በተንጣለለው ግቢ ውስጥ ዓለም የተጠበበችባቸው ከቮልስ ዋግን እስከ ዘመናዊ መኪኖች ረድፍ ሠርተው ተኮልኩለዋል። ሦስቱም በየፊናቸው በግቢው ያለውን እረፍት የለሽ ትእይንት እያደነቁ ወደ አዳራሹ ዘለቁ።

ለምለም ወደ አዳራሹ ለመግባት በማመንታት ወደ ኋላ አፈገፈገች። አዳራሹ በታዳሚዎች መሞላቱ አስፈራት። "በጣም ነው የሚያስፈራው፣ እኔ አልገባም" ብላ ወደ ኋላ ስትመለስ ፌቨን ክንዷን አፈፍ አድርጋ ወደ ራሷ ሳበቻት።

"እኔ ይቅርብኝ። መጀመሪያም አልፈለግሁም ነበር" አለች ለምለም ክንዷን ከፌቨን እጅ ለማስለቀቅ እየሞከረች።

"ገጠሬነትሽን አቁሚ። አጉል መንፈሳዊነትሽን ትተሽ ለዛሬ ቤተ ክርስቲያንን እርሻትና ዘና በይ" አለች ሳምራዊት ቁጣ በተቀላቀለበት ንግግር።

ፌቨን ተበሳጨች። "ዛሬም ከገጠሯ ጎጆሽ አልወጣሽም እንዴ? አሁን እኮ ነፃነት አለሽ፣ ከተማው፣ ጭፈራው አይማርክሽም? በይ አሁን ግቢ" ብላ ወደ ውስጥ እንድትገባ ገፋ አደረገቻት።

ለምለም የደስ ደስ ያላት ጠይም፣ ቀጭን፣ ረጅም ስትሆን አንዲት ለእናቷ የሀገር ባህል ቀሚሷ እስከ ቁልጭምጭሚቷ ሸፍኗታል። "እንዴት ሠርግ ቤት የሀገር ባህል ቀሚስ ትለብሻለሽ?" ብለው ጓደኞቿን ቢያጣጥሉባትም ትችታቸውን ተቋቁማ ነው የለበሰችው።

ለምለም አንድም ቀን እንዲህ ዓይነት ቦታ ላይ እገኛለሁ ብላ አስባ አታውቅም። ተጨነቀች። ወደ ግቢ መመልስ ፈልጋለች ግን በችግሯ የምትደርስላትና ውለታዋ የከበዳት የክፍል ጓደኛዋ የሉሊትን ግብዣ

አልፈልግም ማለት አልቻለችም፡፡ ጓደኛዋንም ማሳዘን አልፈለገችም፡፡ ለምለም ገና ዩኒቨርሲቲ ስትገባ የቀረበቻት ሉሊትን ነው፡፡ ምንም እንኳን የአንድ ማደሪያ ክፍል ተጋሪዎች ባይሆኑም ከፎቶ ኮፒ ጀምሮ ለሚያስፈልጋት ወጪ ሁሉ የምትሸፍንላት ሉሊት ናት፡፡ እንደ ልብ ወዳጅ ነው የምትመለከታት፡፡

ጓደኞቿን ተከትላ ለመግባት ስትሞክር እግሮቿ ተብረከረኩባት፣ ፍርሃት በላይዋ ነገሠ፤ ግን ጓደኞቿን መከተል አላቆመችም፡፡ በአዳራሹ ስፋት፣ በመድረኩ ድምቀት፣ በታዳሚው ብዛት፣ በሽቶው መዓዛ፣ … እየተደነቀች አስተናጋጁንና ጓደኞቿን ተከተለች፡፡ አስተናጋጁ እየመራ ከተዘጋጁት ወንበሮች አረፍ ይሉ ዘንድ ጋበዛቸው፡፡

ለምለም ጎጃም ሞጣ ተወልዳ ያደገች፣ አቅራቢያዋ በሚገኘው አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን በሰ/ት/ቤት ውስጥ በመሳተፍ በአገልግሎት ያለፈች ወጣት ናት፡፡ ቤተሰቦቿን በእርሻ ወቅት በጉልጓሎው፣ በቤት ደግሞ እናቷን በመርዳት በሥነ ምግባር ታንጻ ያደገች ናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመድባ እንደመጣች ነው ግቢ ጉባኤ መከታተል የጀመረችው፡፡ ከትምህርት እና ከመንፈሳዊ ሕይወቷ ውጪ ሌላ ሕይወት የላትም፡፡

ሉሊት የወንድሟን ሠርግ ለማድመቅ መድረኩን ከሚያሳምሩ ባለሙያዎች ጋር አንዳንድ የጎደሉ ነገሮችን በማስተካከል ላይ ሳለች በርቀት እነ ለምለምን ተመለከተች፡፡ በፈገግታ እንደተሞላች መጥታ "እንኳን በደህና መጣችሁ!" ብላ ፌቨንና ሳምራዊትን ስማ ወደ ለምለም እየተመለከተች "ትመጫለሽ ብዬ አልጠበቅሁም ነበር፤ በመምጣትሽ በጣም ደስ ብሎኛል" አለች የለምለምን ጉንጭ እየሳመች፡፡

"እረ ችግር የለውም" አለች ለምለም ለመሳቅ እየሞከረች፡፡

ሉሊት ለምለምን ካየቻት ቀን ጀምሮ ለታናሽ ወንድሟ ሚስት ትሆን ዘንድ ስትመኛት ቆይታለች፡፡ አጋጣሚዎችን ጠብቃ ልታስተዋውቃቸው ብታስብም ሁኔታዎች አልገጥም ብለዋት ቆይቷል፡፡ የክፍል ጓደኞቿ የሀብታም ልጅ መሆኗን ለማሳየት አልፎ አልፎ የእናቷን መኪና ይዛ ግቢ ድረስ ትመጣለች፡፡ ብዙዎቹ ቢከቧትም ግድ አይሰጣትም፡፡ ለምለምን ግን ታቀርባታለች፣ ታዝንላታለችም፡፡ ለምለም ክፍል ውስጥ በዝምታዋ፣ በእርጋታዋና በገጠር የአነጋገር ለዛዋ ትታወቃለች፡፡ ከገጠር ብር ስለማይላክላት የፎቶ ኮፒ፣ የሳሙና፣ የቫዝሊን፣

… ስለሚቸግራት ብዙውን ጊዜ የምትሸፍንላት ሉሊት ናት፡፡ ከሌሎቹ የክፍል ጓደኞቿ ይልቅ ታከብራታለች፡፡

ለምለም በጓደኛዋ አለባበስ ተሳቀቀች፡፡ ከሰውነቷ ጋር የተጣበቀ ጉርድ ሮዝ አጭር ቀሚስ ለብሳለች፣ ከላይ ሮዝ ጡት መያዣ ጣል አድርጋለች፣ አርቲፊሻል ረጅም ጸጉሯ በጀርባዋ ተነስንሷል፡፡ ከዚህ በፊት የምታውቃት ሉሊት አልመስልሽ አለቻት፡፡ ግር ብሏት እያስተዋለቻት ሳለ፡-

“ምነው አለባበሴ አበሳጨሽ እንዴ? የወንድሜ ሠርግ አይደል ከዚህ በላይ የሚያስደስት ምን አለ?” አለች ሉሊት እየሳቀች፡፡ በልቧ ዛሬ ለታናሽ ወንድሟ እንደምታስረክባት እያሰበች፡፡ “አንተ እኮ ብታገባ ምርጥ ባል ነበር የምትሆነው፡፡ እዚህም እዚያም ማለትህን የምታስጥልህ ልጃገረድ ነው የማጋባህ” ትለዋለች ለወንድሟ፡፡

“የገጠር ሴት ካልሆነች አላገባም “ ይላታል፡፡ ጥሎበት የገጠር ልጅ ይወዳል፡፡

“እኔ ምንም አላልኩም” አለች አንገቷን እየደፋች፡፡ ሉሊት ብቻ ሳይሆን አዳራሹ ውስጥ በታደሙት ወጣት ሴቶች አለባበስ እየተገረመች -“እስቲ አሁን እርቃን መሆን ምኑ ነው የሚያስደስተው?” አለች በማጉተምተም፡፡

“ምን አልሽ?” አለች ሉሊት ወደ ለምለም እየተመለከተች፡፡

“ምንም”

“የታክሲ ይዘሻል? በኋላ ግርግሩ ስለሚበዛ በኮንትራት ታክሲ መሄድ ስላለብሽ እሰጥሻለሁ” አለች ሉሊት የለምለምን ስሜት ለመረዳት እየሚከረች፡፡

“እነ ፌቨን አሉ አይደል፣ አብረን አንመለስም እንዴ?” አለች ለምለም በድንጋጤ፡፡

“አረ እንዲህ ዓይነት ግብዣ ተገኝቶ ነው? የዛሬ አዳራችን የት እንደሚሆን አይታወቅም፡፡ ይልቅ በጊዜ ሂጂ” አለች ሳምራዊት እየሳቀች፡፡

“ለምን ትቀልዳለችሁ? አብረን ካልተመለስን እኔ አሁኑኑ መሄድ አለብኝ” አለች ለምለም ፍርሃት እየተነበባት፡፡

“ሙሽሮቹ እንደመጡ ቶሎ ራትሽን በልተሽ ትምለሻለሽ፡፡ እነርሱን ተያቸው ስለማታውቂያቸው ነው፡፡” አለች ሉሊት የለምለምን ፍርሃት ለማቅለል፡፡

ለምለም የሚመቻትን ጥቂት ምግብ አንሥታ ወደ ቦታዋ ተመለሰች ግርግሩ፣ ጫጫታው፣ የሴቶቹ አለባበስ ልተመቻትም፤ ሲያል ውስጥ ያለች መሰላት፡፡

"ተያት እኛን ትምሰል፣ ዓለሟን ትቀጭበት እንጂ" አለች ፌቨን በሳቅ እየተፍነከነከች፡፡

"እናንተ ከተማውን ያሰለቻችሁ ናችሁ፡፡ እርሷ ደግሞ ግራ ቀኙን የማታውቅ ምስኪን ልጃገረድ ናትና ተዋት የመጣችው በእኔ ኃላፊነት ነው እኔው እንደሚሆን አድርጋለሁ" አለች ሉሊት፡፡

ለምለም የክፍል ጓደኞቿ ባሕርይ ተቀያየረባት፡፡ የምታገ ኛቸው ክፍል ውስጥ ነው፡፡ የጋራ የቤት ሥራ ወይም ጥናታዊ ጽሑፍ ሲኖር፣ ከጥናት ጋር ተያይዞ ቤተ መጻሕፍት አብሮ መሄድ ሊሆን ይችላል እንጂ ባሕርያቸውንና ማንነታቸውን አታውቅም፡፡

ሉሊት "መጣን፣ ጠብቁን" ብላ ለምለምን ወደ ውጪ ይዛት ወጣች፡፡ "ወዴት ነው?" አለች ለምለም ግር እያላት፡፡

"አንድ ሰው ላስተዋውቅሽ ከወንድሞቼ አንዱ ነው በኋላ አድርሶሽ ይመለሳል" አለች ግራ ቀኝ እየተመለከተች፡፡

"አያስፈልግም ታክሲ ከያዝኩኝ እኮ እኔ መሄድ እችላለሁ" አለች ለምለም፡፡

"ለምን ትጨናነቂያለሽ? ችግር የለውም፡፡ እንዲያውም ያውና" ብላ እጇን እያወራጨች ምልክት ሰጠችው፡፡ ዳዊት አላመነታም በፍጥነት መጣ፡፡ "ዳዊት ይባላል ወንድሜ ነው ተዋወቁ" አለች፡፡

ለምለም በአክብሮት በሁለት እጆቿ እየጨበጠችው “ለምለም እባላለሁ” አለች፡፡

“ዳዊት እባላለሁ፡፡ ስለተዋወቅሁሽ ደስ ብሎኛል” አለ በፈገግታ፡፡

“እራት ከበላች በኋላ ግቢ ታደርሳታለህ፡፡ እግረ መንገድህንም ትጋብዛታለህ” አለች ሉሊት እየጠቀሰችው፡፡

ዳዊት ገብቶታል፡፡ ወዲህ ወዲያ ስል እንዳልረሳ፤ መሄድ ስትፈልጊ ደውይልኝ” ብሎ ስልክ ቁጥሩን ሰጣት፣ የእርሷንም ተቀበለ፡፡

ሙሽሮች በመምጣታቸው ሉሊትና ዳዊት ለመቀበል ሲወጡ ለምለም ወደ ጓደኞቿ ብትመለስም ልታገኛቸው አልቻለችም፡፡ ተደናገጠች፡፡ አዳራሹን በዓይኖቿ ስትቃኝ አራት ከሚደርሱ ወንዶች ጋር እየጠጡ ሲሳሳቁ ተመለከተች፡፡ ፈራች፤ መሄድ ብትፈልግም በቂ ገንዘብ የላትም፡፡ ግራ ቢገባት አንድ ጥግ ላይ ቆመች፡፡ አዳራሹ በአጃቢዎች ጭፈራና ሆታ ድብልቅልቁ ወጣ፡፡ የሚጎነትሏት፣ በዓይናቸው እየጠቀሱ የሚያባብሏት ወንዶች ፋታ ነሿት፡፡

ለምለም አንድ ወንበር ስባ ብቻዋን ጥግ ላይ ተቀመጠች፡፡ ምግብ ሙሽሮቹ ካነሡ በኋላ ከፊት ያሉት አጃቢዎች ሲነሡ ሉሊት ለምለምን ፈልጋ አገኘቻት፡፡ “ለምን ብቻሽን ተቀመጥሽ? እነ ሳምሪ የት ናቸው?” አለች፡፡

“እኔ እንጃ፤ አጣኋቸው” አለች ለምለም በፍርሃት፡፡

“በይ ነይ ራት በልተሽ ትሄጃለሽ” ብላ እጇን ይዛ ሰልፍ የያዙትን ሰዎች አልፋ ከተዘጋጀው ምግብ ላይ እንድታነሣ ጋበዘቻት፡፡ ለምለም የሚመቻትን ጥቂት ምግብ አንሥታ ወደ ቦታዋ ተመለሰች፡፡ ግርግሩ፣ ጫጫታው፣ የሴቶቹ አለባበስ አልተመቻትም፤ ሲኦል ውስጥ ያለች መሰላት፡፡

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ሉሊት ከወንድሟ ዳዊት ጋር ወደ ለምለም መጣች፡፡ “በል እንግዲህ ፈረሱም ሜዳውም ይኸው” አለችው የዳዊትን ትከሻ መታ መታ እያደረገች፡፡ “በሉ ሂዱ፡፡ ደህና እደሪ” አለች ሉሊት ወደ መስተንግዶዋ እየተመለሰች፡፡

“ከጨረስሽ እንሂድ” አለ ዳዊት በዓይኖቹ ለምለምን ከእግር እስከ ራሷ አገላብጦ እያያት፡፡

ለምለም የዳዊት ዕይታ አስፈራት፡፡ ነገር ግን “ዳዊት ማለት ሉሊት ማለት ነው፤ ምን ያስፈራኛል?” አለች ለራሷ፡፡

“እሺ እንሂድ!” ብላ መንገድ ጀመረች፤ ዳዊት ተከተላት፡፡ ከአዳራሹ ስትወጣ ከሲያል ወላፈንና ጨኸት ያመለጠች ያህል እፎይታ ተሰማት፡፡ ሰዓቷን ስትመለከት ለሦስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሆኗል፡፡ በየጊዜው ከምሽቱ ሦስት ሰዓት የምታደርሰው የመኝታ ጸሎቷ እንዲታጎልባት አልፈለገችም፡፡

ዳዊት መኪናውን ወደ ደብረ ዘይት አስከነፈው፡፡ ለምለም የመኪናው ፍጥነት፣ አቅጣጫውም ወዴት እንደሚሄድ ግራ አጋባት፡፡

“በእናትህ ፍጥነቱን ቀንሰው፤ ወዴትስ ነው የምንሄደው?” አለች በፍርሃት፡፡

ዳዊት መልስ አልመለሰላትም፡፡

“እባክህ አቁመው፤ ከከተማ እየወጣን እኮ ነው፡፡ ወዴት ነው የምትወስደኝ?” አለች በጭቀት፡፡

“እንመለሳለን፡፡ አንድ እቃ ገዝቼ መመለስ አለብኝ” አላት ዳዊት በእርጋታ፡፡

“አልፈልግም መልሰኝ” በሩን ለመክፍት ስትሞክር በአውቶማቲክ መቆለፊያ ዘጋው፡፡

“ምን እያደረግህ ነው?”

“ምንም፡፡ እንመለሳለን አልኩሽ፡፡”

ወደ ደብረ ዘይት መንገድ መውጫ ጫፍ ላይ ከሚገኘው ዘመናዊ ሆቴል ግቢ ውስጥ መኪናውን አስገብቶ “ወረጂ!” አለ ፊት እየነሣት፡፡ አውሬው ጥፍሩን አሹሎ፣ ጥርሱን አግጥጦ የመጣባት ያህል ደነገጠች፤ ለማምለጥ በሩን ከፍታ ሮጠች፡፡ ነገር ግን የትም መድረስ አልቻለችም፡፡ በአንድ ጥፊ ከመሬት ደባለቃት፡፡ ለምለም ሰማይ ምድሩ ዞረባት፡፡ “ሜዳውም፣ ፈረሱም ይኸው!” የሚለው የሉሊት ድምጽ በጆሮዋ መልሶ መላልሶ አስተጋባ፡፡ መሬት ላይ እንደ ወደቀች “ወይኔ እናቴ ማርያም፤ እባክሽ አድኚኝ” ብላ ምርር ብላ አለቀሰች፡፡

ዳዊት እኅቱ ስለ ለምለም ሁል ጊዜ ስለምትነግረው በአካል ሳያውቃት ነው የወደዳት፡፡ የከተማ ሴቶች አይመቹትም፡፡ በሥራ ምክንያት ወደ ገጠር ከገባ ከገጠር ልጃገረዶች ጋር ልቡ ይሸፍታል፡፡ ያልተነካችውን ነው የማገባው”

ይላል፡፡ ይህንን ፍላጎቱ የምታሟላው ደግሞ በሉሊት ዕይታ ለምለም ብቻ ናት፡፡ እናም ለወንድሟ አሳልፋ ሰጠቻት፡፡

ለምለም ለማምለጥ አቅም አልነበራትምና ዳዊት ጎትቶ አነሣት፡፡ ከጎኑ የታጠቀውን ሽጉጥ ሽንጧ ላይ ደግኖ "እጮኻለሁ ወይም አመልጣለሁ ብትይ ግንባርሽን ነው የምበትነው ቀጥ ብለሽ ግቢ" አለ ከሆቴሉ ወደ አስያዘው ክፍል እየገፋት፡፡

ለምለም ምርጫ አልነበራትም፤ እያነባች እንደ ከብት ተነዳችለት፡፡ -"ፈረሱም ሜዳውም ይኸው!" የሉሊት ድምጽ ጆሮዋ ላይ ያስተጋባል፡፡ አባባሏ ተንኮል እንደነበረው የተረዳችው ዘግይታ በመሆኑ በራሷ ተናደደች፡፡

ዳዊት ቸኩሏል፤ ወደያዘው ክፍል አስገብቶ አልጋ ላይ ወረወራት፡፡ በእጁ የገባችውን እምቡጥ ጽጌረዳን ለመቅጠፍ ተጣደፈ፡፡ በዚህ ቅጽበት ለምለም ከአልጋው አጠገብ ያለውን የራስጌ መብራት አንሥታ ዳዊት ጭንቅላት ላይ አሳረፈችው፡፡ ዳዊት ደም አስክሮት ተዝለፍልፎ ሲወድቅ ለምለም በሩን ከፍታ ወደ ውጪ ሮጠች፡፡

"ምን ሆነሽ ነው? ወዴት ነው በዚህ ሰዓት?" በሩ ላይ የነበረው ጥበቃ በለምለም ችኮላ ተጠራጥሮ ጠየቃት፡፡

"መጣሁ - እዚህ ..." ምላሿን አልጨረሰችም፤ እግሯ ወደመራት ሮጠች፡፡ ለምን ያህል ደቂቃ፣ ወደ የት እንደሮጠች አታውቀውም፡፡ ከፊት ለፊቷ ባልና ሚስት የመንገዱን ጠርዝ ይዘው እየተሳሳቁ ሲሄዱ ያድኗት ዘንድ ከሠርግ ሲመለሱ ሩጫዋን ገታ አድርጋ "አድኑኝ! አድኑኝ!" ብላ ሴቷ ላይ ተጠመጠመች፡፡

"ምን ሆነሽ ነው ልጄ? ሁለቱም ደንግጠው ጠየቋት፡፡

ለምለም እያለቀሰች "ብቻ የዛሬን አድኑኝ፤ እማማ ከአውሬው አድኑኝ" አለች ከአቀፈቻቸው እናት አጠገብ መሬቱ ላይ እየተቀመጠች፡፡

ባልየው በተጎነጩት የአልኮል መጠጥ ሞቅ ብሏቸዋል፡፡ ሙሉ ሱፍ ከነከረባቱ፣ ሚስት ደግሞ የሀገር ባህል ልብስ ለብሰዋል፡፡ "ከጎረምሶች ጋር ስትዛለል ቆይታ ይሆናል" አሉ ለምለምን በጥርጣሬ እየተመለከቱ፡፡

"እስቲ ዝም በል እኛም እኮ ልጆች ወልደናል ነግ በእኔ ነው" አሉ ሚስት ለምለምን በፍቅር እየተመለከቷት፡፡

“የዘንድሮ ልጆች ምናቸው ይታመናል?” አሉ በግድ የለሽነት፡፡

“ምን አለበት ዝም ብትል” አሉ ሴትየዋ በባለቤታቸው አነጋገር ተበሳጭተው፡፡

“የዘንድሮ ልጆች መቼ ሰው የሚላቸውን ይሰማሉ፡፡ ልባቸው ያሰበውን ካልፈጸሙ አያርፉም እኮ፡፡”

“እስቲ ዝም በል! ምን እንደገጠማት በምን አወቅህ? ነይ የኔ ልጅ ወደ ቤት እንሂድ፣ ራስሽንም አረጋጊ” ብለው ከተቀመጠችበት አነሷት፡፡ “እኛም አንቺን የምታህል ልጅ አለችን፡፡ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ነው የምትማረውና ምን እንደሚገጥማት እኔ በምን አውቃለሁ፤ ልጄን አስታወስሽኝ፡፡ እኔን እናትሽ! ጠንከር በይ የኔ ልጅ” አሉ ጭንቅላቷን እያሻሹ፡፡

ለምለም ራሷን ለማረጋጋት ጊዜ ቢወስድባትም ባልና ሚስትን ተከትላ ወደ ቤታቸው እየሄዱ ሳለ የገጠማትን ሁሉ ነገረቻቸው፡፡

“አይዞሽ አትፍሪ ዋናው እንኳን እግዚአብሔር አተረፈሽ፡፡ ባለን ነገር ሁሉ እንረዳሻለን፡፡ ወደፊትም ተጠንቀቂ” አሏት፡፡

“እሺ እማማ! እንደማይመስሉኝ እያወቅሁ እኮ ነው የቀረብኳቸው፡፡ ቢሆንም ሉሊት ለእኔ ጥሩ ሰው ነበረች እኮ! እንዲህ አሳልፋ ትሰጠኛለች ብዬ መች አሰብሁ? ለካ ከመንገዴ ልታሰናክለኝ ጉድጓድ ስትቆፍርልኝ ኖሯል?” አለች ለምለም በጸጸት፡፡

“ልጄ እንኳንም እግዚአብሔር አተረፈሽ፡፡ አሁንም አንቺን ከማይመስሉ ጋር አትዋዪ፣ አትቅረቢያቸውም፡፡ መሰናከያው ብዙ ነውና ስንት ልጆች ወጥተው ቀርተዋል መሰለሽ? ከማይመስሉሽ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመጂ” አሏት፡፡

“አይለመደኝም እማማ፣ በጣም አመሰግናለሁ፡፡” አለች ለምለም ካጋጠማት ክፉ ነገር ያወጣትን እግዚአብሔርን እያመሰገነች ተከተለቻቸው፡፡